Bethel Belete
1/8/12 (214) 405-2089

# በቋጥኝ ላይ የበቀለች ዋርካ

የነብይ ገርባሌ ሂርጳ የህይወትና የአገልግሎት ታሪክ

በደረጀ በቀለ

2003 ዓ.ም

ኑብይ ገርበሌ ሂርጳ 2003 ዓ.ም

© ያለ አሳታሚው ፈቃድ እንደገና ማሳተምም ሆነ ወይም በሌላ በማናቸውም

መንገድ ማቅረብ በህግ የተከለከለ ነው።



ኑብይ ገርበሌ ሂርጳ

የሽፋን ዲዛይን እና የኮምፒውተር ጽሑፍ፡- ወ/ሮ ትደነቅ ታሪኩ

# ምስጋና

ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ በኔ በተራው ሰው ክብሩን ከገለጠው ጌታ ባሻገር በርካታ ላመሰግናቸው የሚገባ ሰዎች አሉ፡፡ ከልጅነት ጅምሮ በስደት በነበርኩባቸው ዓመታት በማንኛውም መንገድ ከኔ ጋር ለቆሙት ወገኖች፣ በመቀጠልም በብዙ ውጣ ውረድ የመከራ ዓመታት የቤተሰቤን ሸክም ለብቻዋ በመሸከም ያለትካዜ እንዳገለግል "ለኛ አታስብ በሰላም ሂድና አገልግል" በማለት ልጆችን በማሳደግ እንግዳ፣ በመቀበል በአገልግሎቴ በመደገፍ ለአገልጋይ ሚስቶች ምሳሌ መሆን ለምትችለው ለምወዳት ባለቤቴ ለአዳነች ቶሌራ፣ ለእግዚአብሔር ክብርና ለሌሎችም ትምህርት ይሆናል በማለት ይህን መጽሐፍ ለዓፊው ለደረጃ በቀለና ለባለቤቱ ለታደለች ደገፉ፣ ተፈሪ መርጋ፣ የሶርስ ኦፍ ላይት ሚኒስትሪስ ኢትዮጵያ ዳሬክተር ኃይለስላሴ ተፈራ ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው ረቂቁን በማንበብ አስተያየታቸውን ለሰጡን ለዶ/ር ንጉሴ ተፈራ፣ ለፓ/ር በቀለ ወልደኪዳን እና ለፓ/ር ጻድቁ አብዶ የህይወት ዘመን ታሪክ ስለሆነ ወደኋላ ተመልሰው ስለኔ የሚያውቁትን በጽሑፍም በስልክም መረጃ ለሰጡ ሁሉ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ የብዙዎቻችሁ አስተያየት በመዲጋገሙና ከቦታ ጥበት የተነሳ ባይወጣም አስተዋፅዖአችሁ ግን አይረሳም፡፡ እና የሽፋን ዲዛይንና የኮምፒውተር ጽሑፉን ለሠራችው ለትደነቅ ታሪኩ ምሥጋናዬ የላቀ ነው፡፡

## መታሰቢያነቱ

በየዘመኑ ስለ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መላ ዘመናቸውን ከዚያም አልፎ ሕይወታቸውን ለከፈሉ ከደብረብርሃኑ አስጢፋኖስ እስከ አጋዴኑ አስጢፋኖስና ለሌሎችም ኢትጵያውያን የወንጌል ሰማዕታት በሙሉ፡፡

ጥቅሶቹ የተወሰዱት በ1954 ዓ.ም ከታተመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡

## መግቢያ

በሀገራችን ታሪክ አይፃፍም፡፡ የተለመደ አይደለም፡፡ ሰዎች ይመጣሉ ይሄዳሉ፡፡ ክስተቶች ይፈጠራሉ ያልፋሉ፡፡ ትተውት ከሄዱት አሻራ ለመማር መለስ ብለን አናያቸውም፡፡ የዘመናቸውን እሽክርክሪት ጨርሰው ያልፋሉ፡፡ ተጠግተን ሳናያቸው ያልፋሉ፡፡ እንደምንም ፈጥነን ልንደርስባቸው ከሞከርን ሲቀበሩ እንደርስና አፈር ሲመለሰባቸው ፓስታው ሲታሽግ "ጥሩ ሰው ለብዙዎች ምሳሌ የሚሆን ተግባቢ ወዘተ" ሲነበብ እንደርሳለን፡፡ እኛም ደብቀን ያኖርነውን የዚያን ሰው መልካምነት በሌለበት እንሰማለን፡፡ በህይወት እያለ ያላየንለትን ሩጫውን ሲያበቃ እንናገርለታለን፡፡ በመጨረሻዋ ሰዓት እንዲህና እንዲያ ነበር ብለን እንበታተንና እየዋለ እየደረ ከትዝታነትም እያለፈ ለዘላለሙ ይረሳል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በሰዎች ያደረጋቸው ድርጊቶች ታሪክና ዘገባ ጥምር ነው፡፡ ዘፍጥረት የመፅሐፍ ቅዱሳችን አንዱ መፅሐፍ ነው የአብርሃምና የልጆቹም የህዝበ እስራኤልም ታሪክ ነው፡፡ በዚያም ላይ የታላቁ አምላካችን ድንቅ አሠራር ሚስጥር ነው፡፡ በዚሁ አይነት የነብዩ ገርቦሌ የህይወትና የአገልግሎት ታሪክ የግለሰቡም የእግዚአብሔርም ድንቅና ሀያው ሥራ ታሪክ ነው፡፡ አንዱን ካንዱ ለይተን አናየውም ከዚህ የተነሳ እንደልማዳችን ገርቦሌን ስንሰናበት ከምናነበው ቀደም ብዬ እግዚአብሔር በግለሰቡ ሕይወት ያደረገውን ከልጅነት እስከ ሽበት የግለሰቡንም የታማኝነት ምላሽ ለመፃፍ ሞክሬያለሁ፡፡ በዚህም እግዚአብሔር ዛሬም ቅርብና በመካከላችን የሚሰራ መሆኑን በአንድ በኩል በሌላ በኩል ደግሞ ለእግዚአብሔር ከኛ ጋር መሥራት የኛን ታማኝነት አስፈላጊነት በማሳየት ሚዛኑን ለመጠበቅና ለማጣጣም ሞክሬያለሁ፡፡

በመጨረሻም ይህ የእግዚአብሄር ሰው ጌታን በፊት ለፊት እያየና እያነጋገረ እስከዛሬም ድረስ ባለፉት ሰላሳ ሰባት ዓመታት

# "እሙሩ ላይ እግዚአብሔር ወረደ"

ብዙ ጊዜ ቀዝቃዛ ከሆኑ ሰዎች ይልቅ ተግባራዊ የሆኑና በእንቅስቃሴ የተሞላች ነፍስ ያላቸው ሰዎች ከተለወጡ በኋላ እንኳ የተሻለ እግዚአብሔርን የማገልገልና ግዴታቸውን የመወጣት ሁኔታ ይታይባቸዋል፡፡ ለምሳሌ ሐዋርያው ጳውሎስ አሳዳጅ በነበረበት ጊዜ ሸኚ ደብዳቤ ብቻ ቢያገኝ በራሱ ወጪ የኢየሱስን ተከታዮች እስከ ሩቅ ድረስ በመሄድ ለማጥፋት የወሰነ ሰው ነበረ፡፡ ከሮም መንግስት ወይም ከአይሁድ ካህናት ሳይላክ በራሱ ተነሳሽነት በራሱ መጓጓዣና ስንቅ በራሱ አጃቢና ፈረስ ወደ ደማስቆ ገሰገሰ፡፡ በዚሁ መሠረት በራሱ ወጪ በራሱ ስንቅ ወንጌልን ይዞ ሩቅ ድረስ ተላከ፡፡ በዚህ አይነት ብዙ ሰዎችን እናገኛለን ለራሳቸው ጉዳይ ታታሪ የነበሩና ወደጌታ ሲመጡ ታታሪነታቸውን ለመልካም ነገር በመለወጥ ታላላቅ ሥራ የሰሩ አባ ሮሮ ዋጣ ከነዚህ አይነት ሰዎች ይመደባሉ፡፡

ወጣቱ ሮሮ ዋጣ ተወልዶ ባደገበት ጎጃም ክፍለሀገር የዘውድ ስርዓት በድሀው ገበሬ ላይ የሚያደርሰውን ግፍ መታገስ አልቻለም፡፡ ለገበሬው ልጆች ት/ቤት አለመኖር ለህሙማን የህክምና አገልግሎት መጓደል ጎልቶ ታየው፡፡ ይህ የህዝብ ጉስቁልና ሸክም ሆነበት ሕይወቴን ለክበረ ነገር ማዋል ካለብኝ ይህን ህዝብ ከዚህ አገዛዝ ነፃ ለማውጣት መሆን አለበት በማለት ሸፍቶ ጫካ ገባ፡፡ ከመሰሎቹ ጋር በዱር በገደል ተገናኝተው ሁለት ወረዳዎችን ከንጉሱ አስተዳደር ነፃ አውጥተው በ1941 እና በ1942 ዓ.ም ለሁለት አመት በራሳቸው አመራር አስተዳደሩ፡፡ ነገር ግን እንዲህ ድል እየቀናቸው ባለበት

ሰዓት የሰውን ሁሉ አካሄድ በሚወስነው አምላክ ባልታ ግብነት ከጫካ ወጥቶ ወደ ቤተሰቡ በመመለስ መኖር ጀመረ፡፡ ሚስት አግብቶ በሰላም እየኖረ እያለ ወደ ወሊጋ ክፍለ ሀገር ተሻግሮ በግብርና ሥራ ተሰማራ ትልቅ ሰውም ሆነ፡፡

በ1960 ዓ.ም በታህሳስ ወር አንድ ህልም አለሙ፡፡ ባሉበት አገር ላይ ከሰማይ ትልልቅ ድንጋይ የሚያህል ድቡልቡል እሳት ሲወድቅ ሣር ቅጠሉ እየተያያዘ ሲነድ አዩ፡፡ የእሳቱ ኳስ እርሳቸውም ላይ ወድቆ እንዳይቃጠሉ በህልማቸው ወደ ወንዝ ሮጡ፡፡ እሳቱ ድንገት ቢወድቅባቸው ወደውሀው ውስጥ ጥልቅ በማለት ከመቃጠል ለመትረፍ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ እንዳሰቡት ውሀ ውስጥ ሳይገቡ እሳቱ አረፈባቸው፡፡ የማይጎዳ ደስ የሚያሰኝ ህልውና ያለው የሰላም እሳት እንጂ እንደሚያውቁት የምድጃ እሳት ሆኖ ስላላገኙት ወደዱት፡፡ በዚያው ሰሞን ቀደም ሲል ታሞ በየቃልቻው ቤት ይወስድ የነበረ ልጃቸውን ይዘው እነ አቶ መኩሪያ ሙሉጌታ ወደሚፀልዩበት ቦታ በመሄድ ልጁም ዳነ እርሳቸውም ንስሀ ገብተው በጌታ አመኑ፡፡

እኚህ ሰው ቀድሞም ነፃነት ላጣ ተቆርቋሪ ነበሩና ትክክለኛውን ነፃ አውጪ ሲያገኙ ተጣበቁበት በፆም በፀሎት በአገልግሎት በረቱ በሚያውቁት ስርጓትጥና ስርጥ እያሳበሩ ጎጃም ድረስ በመሻገር ወንጌልን ሰበኩ፡፡ ጌታም አብሯቸው ነበርና በሄዱበት ድንቅና ታምራት ያጅባቸው ነበር፡፡ በህልም እንዳዩትም በአገሩ ላይ ትልልቅ ሥራ የሚሠራ ትልልቅ እሳት ወረደ እኚህም ሰው የዚህ እሳት ታታሪ አገልጋይ ለመሆን በሬዎቻቸውን ፈተው





ሞፈራቸውን ሰቅለው እንደመደበኛ አገልጋይ መሰማራት ጀመሩ፡፡ ወደ ጎጃም ተሻግረው የተደረገውን ድንቅ የሰሙ ተከትለዋቸው ወሊጋ ድረስ ይመጡ ነበር፡፡ ከ50 እስከ 60 የሚደርስ ሰው ከሀመሙ ለመፈወስ አባይን በዋና በመሻገር "አንድ መፅሐፍ በእጁ ይዞ የሚዞር ሰው አይታችኋል ወይ" በማለት ያፈላልጉና ያገኟቸዋል፡፡ ለተናጠል ህመማን ብቻ ሳይሆን በተስቦ ለተወረረ መንደር ሄደ በመፀለይ ወረርሽኝ ከገባበት አካባቢ ለመድሀኒትነት ተልከባቸው ይሄዱ ነበር፡፡ ሞትን ከያገሩ ያባርሩም ነበር፡፡

ቀስ በቀስም ከአዲስ አበባ ከሚሄዱ አገልጋዮች ጋር በመገናኘት ሰፋ ያለ የወንጌል ሥራ ሠርተዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ አንዱ ዶ/ር ኃይሌ ወ/ሚካኤል ሲሆኑ ስለወንጌል ታስረው ዋስ የሆነው ካስፈቷቸው በኋላ አብረው አገልግለዋል "አንድ ጊዜ ለአገልግሎት ስንጓዝ" ይላሉ አባባ ሮሮ "የጅብ መንጋ ከበበን ብዛት የነበረውና የተቆጣ ስለነበር እንደሚያጠቃን ተረዳን፡፡ ይህ የሆነው ቅጠል እንጥፈን ከተኛንበት ዛፍ ሥር ሌሊት ላይ ነው፡፡ ዶ/ር ኃይሌ የጌታን ስም ሲጠራ የከበቡን ጅቦች ተበታተኑ፡፡

ሌላ ጊዜ በበጋ ወራት በጠራራ ፀሐይ በጫካ እየተጓዝን ሳለ የሰደድ እሳት ተነስቶ በዙሪያችን ያለው ደን ተያያዘና እኛ እሳቱ መሀል ተቆርጠን ቀረን፡፡ ሁለታችንም የጌታን ስም ስንጠራ የእሳቱ ምላስ እየተሰበሰበ ጭስ ብቻ ሆነ በጭሱ ውስጥ ተጉዘን ወጣን" ያን ጊዜ የዳኑ ሁሉ በጌታ ስም ታላላቅ ተዓምር ያደርጉ ነበር፡፡ ለምሳሌ ዘሪቱ የምትባል በውበትና በሀብት የታወቀች ሴት ነበረች፡፡ ይህች

ሴት ባላባቶችንና ሹማምንቱን በመጻፏ ውስጥ በማስገባት ባገሩ ላይ ገና ሳለ ጌታ ኢየሱስን አወቀች፡፡ ዳነች፡፡ ስለጌታ መመስከር ጀመረች በውበቷ ይነሆልሉ ለነበሩ ሁሉ የጌታ መንፈስ በኃይል ይሠራበት ነበር፡፡ አጋንንት ይወጣሉ በሽተኞች ይፈወሳሉ፡፡ ሥራ የበዛላት ሴት ሆነች፡፡ እንግዲህ እነዚህና ሌሎችም ሁሉ የሚቆሰቁሱት እሳት ፍንጣሪ ነው ወደ ኢበንቱ ወደገርቦሌ የደረሰው በዚያ ዘመን የእግዚአብሔር ጉብኝት ውጤት ነው ገርቦሌና አገልግሎቱ፡፡ ከዚህም ባለፈ ከ1960 ጀምሮ በሆሮ ጉድሩ የታየው የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ በጣም ሰፊና አገሩን ያዳረሰ ሲሆን በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲህ ያለ ሰፊ የእግዚአብሔር ጉብኝት አልታየም፡፡ በርግጥ በሚያምኑ ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ጣት ብትመጣም እንደ አባታችን ሮሮ ዋጣ ህልም እሳት ከሰማይ በስፋት የወረደበት ቦታ የለም፡፡ ስለሆነም በኢትዮጵያ ከታየው የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ የሆሮ ጉድሩው የተለየ ነበር ማለት ይቻላል፡፡





# የልጅነት ዘመን

ከቀድሞ የወለጋ ጠቅላይ ግዛት አውራጃዎች አንዱ ሆሮ ጉድሩ ሲሆን ኢበንቱ በዚያ ከሚገኙ ወረዳዎች አንዷ ናት፡፡ ኢንዴ የወረዳዋ ዋና ከተማ በመሆን በደረጃዋ የመንግስት አስተዳደር አገልግሎቶችን ማለትም ፖሊስ ት/ቤት ፍ/ቤት አስተዳደር አነስተኛ ክሊኒክ የምትሰጥ ከተማ ናት፡፡ ሆሮሬሙ ደግሞ በወረዳዋ ውስጥ ከሚገኙ ብዙ ቀበሌዎች አንዷ ናት፡፡

ይህ አካባቢ ወይናደጋማ የአየር ንብረት ያለው ሲሆን የመሬቱም አቀማመጥ ወጣ ገባ እና ሜዳማ ነው፡፡ ሜዳማው መሬት በሣርና በእርሻ የተሸፈነ ሲሆን ወጣገባው ሸለቋማውና ወንዛ ወንዙ ደጋማ ነው፡፡ ሾላ፣ ዶቆማ፣ እንጆሪ፣ ኢጋም፣ ቀጋና ዋርካ በዚያ ይገኛሉ፡፡ ደጋጉሌ ለገዳቢና ደገአፊሰ ከትላልቆቹ ወንዞች ይቆጠራሉ፡፡ ከሚነሱባቸው ተራራዎች ጀምረው እስከ መዳረሻቸው አባይ ድረስ ደኑን ሰንጥቀው ፀሐይ ሳይመታቸው ንፁህና ቀዝቃዛ ውሃቸው የተጠማውን ሁሉ እያረካ በጎደለ ከገባር ምንጮች ከንዳቸውን እያፈረጠሙ በገደላማ መልካዎች ላይ የሚወረወሩ ፏፏቴዎች በመስራት ይወርዳሉ፣ ይሄዳሉ፣ ዝንት ዓለም ይሄዳሉ፡፡ ከሚያዝያ ማለቂያ እስከ ጥቅምት መጨረሻ በሚዘልቀው ረጅም የዝናብ ወቅት በሚገኘው ሰማያዊ በረከት ምድሩ ሕይወት ይፀንሳል፡፡ ሕይወት ያበቅላል፡፡ ሕይወት ያፈራል፡፡ በጫካዎቹ እንደ ነብር፣ ጅብ፣ ሚዳቋ፣ ጦጣ፣ ዝንጀሮ፣ ጉሬዛ፣ አሳማና ልዩ ልዩ አእዋፋት ይመሰጋሉ፡፡ ለሣሩ ዝናብ፣ ለድኩላው ማር፣ ለነብሩ ድኩላ

ያልተዛባ ተፈጥሮ ሚዛኗን ጠብቃ ለሁሉም ወገን የታጨቀ ምግብና የሞቀ መሰማሪያ በመኖሩ በዚያ ሕይወት ሰላም ነው፡፡

የጫካውን ዳር የሚዳውን ጥግ ይዘው የተሰሩ የሣር ክዳን ቤቶች በተናጠልና በቡድን እዚያና እዚህ ከሚታዩት እርሻዎች ጋር ተጋጥመው ይታያሉ፡፡ በተለይ ጧትና ወደ ማታ ከሣር ቤቶቹ ውስጥ የሚወጣው ጢስ የእከሌ ቤት ብሎ ለማሳየት በሩቁ እንደምስሶ ሲወጣና ሲበተን ይታያል፡፡ ባካባቢው የሚበርቁ ጥጆች ርቀው የማይሄዱ ግልገሎች ጓሮ የሚጭሩ የሚያስካኩ ዶሮዎች ለቀዬው ድምቀት ናቸው፡፡ በጓሮ ድንች ሽንኩርት በቆሎና ጎመን ይበቅላል፡፡ ወደ እርሻ ሲወጣ ጤፍ፣ ዳጉሳ፣ አተር፣ ባቄላ፣ ስንዴ፣ ገብስና የመሳሰሉት ይገኛሉ፡፡

በአጠቃላይ የምድሩ ባለፀግነት ከስልጣኔ በቀር ያ አካባቢ ምንም የማይጎድለውና የታደለ ለመሆኑ ምስክር ነው፡፡

አቦ ሂርጳ ቆጨና አዴ ተረፈች ቤኛ ኑሯቸውን በዚሁ ምድር በረከት ላይ አድርገው ትዳር መስርተው የወለዱ የከበዱ የአካባቢው ነዋሪዎች ናቸው፡፡ ቤቱ በህፃንነት የሞቱትንም ያደጉትንም ጨምሮ ስድስት ወንድና ሦስት ሴቶች በአጠቃላይ ዘጠኝ ልጅ የተወለደበት ያራስ ቤት ነው፡፡ አዴ ተረፈች ስምንት ጊዜ አምጠው ዘጠኝ ልጅ ያገኙት ገርቢና ገርባሴ ያሏቸውን ልጆች በመንታነት ስለወለዱ ነው፡፡ ያም በ1954 መሆኑ ነው፡፡ ሴቷ ገርቢ ሳታድግ በህፃንነት ስትሞት ወንዱ ገርባሴ አደገ፡፡ ዘጠኝ አመት ሲሆነው የበግ መንጋ ተከትሎና ሀላፊነት ወስዶ ለጥበቃ ወደ መስክ ወጣ፡፡ በተጓዳኝም





ውሃ ከምንጭ በቅል ወይ በማንቆርቆሪያ በመቅዳት ለእናቱ ያቀርባል፡፡ በአባቱም በኩል ቢሆን የሚመረጥበትና ከሌሎቹ ልጆች ይልቅ የሚፈለግባቸው አገልግሎቶች ነበሩ፡፡ ሲልኩት ፈጣንና መልዕክቱን በትክክል በማድረስ የልብ የሚያደርስ ልጅ ነው፡፡ መልዕክት አድራሽ ብቻ ሳይሆን የልብ አድራሽ ጭምር ነበር ማለት ነው፡፡ አቦ ሂርጳ ደግና ሩህሩህ ሰው ስለነበሩ ለተቸገሩ የሚያዝኑና የሚረዱ በአካባቢው የሚወደዱና የተከበሩ መካከለኛ ኑሮ የሚኖሩ ጎበዝ ገበሬ ናቸው፡፡ እህል ከአውድማ ቋጥረው ጧሪ ለሌላቸው ወይ የአካል ጉዳተኛ ለሆኑ ሰዎች በገርባሴ ይልካሉ፡፡ በማታ ወይ በማለዳ በሚስጥር ነው የሚልኩት፡፡ ገርባሴም ያደርሳል ሚስጥሩም ይጠበቃል፡፡

በዚሁ በተለመደው የየዕለት ኑሮ ሂደት ውስጥ እያለ በ1965 ዓ.ም ይህ ልጅ በአሥራ አንድ አመቱ በመስክ በጎች እየሰማራ አእምሮው ለተፈጥሮ መገኘት ምክንያታዊ ምላሽና መነሻ ስለመኖሩ የማያቋርጥ ጥያቄ ያነሳ ጀመር፡፡ "ተራራና ወንዙን ማን ፈጠራቸው? ውሃውስ ያለ ማቋረጥ በቁልቁለት እንዲሮጥ ማነው የሚነዳው? በጎቹ የሚበሉት የሜዳው ሣር በየቀኑ እየተበላ በማግስቱ አድጎ የማገኘው እንዴት ነው?" በማለት ስለሰማይ ወፎች ኑሮና ውበት ስለ ዱር እንስሳት ሁኔታ ብቻውን በመጠየቅና በመገረም መዋል አመጣ፡፡ ጥያቄ በጥያቄ የሆነው ይህ ልጅ ከማሰላሰል አልፎ ጨዋታ አያምረውም ከሌሎች እረኞችም ጋር አይደባለቅም፡፡ ሲያውጠነጥን ውሎ ይመሻል፡፡

ከእለታት አንድ ቀን እንደ ወትሮው ሁሉ ብቻውን በሜዳ ከበጎቹ ጋር ሳለ አንድ ሰው ወደ እሱ መጣ። በጣም ውብ ነው ፀጉሩ ረጅም ሲሆን የሚሄደው እንደ ገርበሴ በባዶ እግሩ ነው። ያም ሆኖ እግሮቹ ያካባቢው አቧራና ጭቃ የነካው አይመስለም ውብና ንፁህ ናቸው። ያም ሰው ወደ ገርበሴ ቀርቦ ብቻህን ስለሆንክ ጓደኛ ልሆንህ መጣሁ አለው። ልጁም ጓደኛ ስላልነበረው በጣም ደስ አለውና "ከኔ ጋር ትቆያለህ" በማለት በጉጉት ሲጠይቀው እንግዳው ሰው በሚማርክ ፈገግታ "እኔ እወድሃለሁ ጓደኛም እሆንሀለሁ አልለይህም" በማለት ለዘለቄታው የሚቆይ ወዳጅ መሆኑን ያረጋግጥለታል። ልጁ ስለ አዲሱ ጓደኛው የበለጠ ለማወቅ "አንተ ማነህ? ከየት መጣህ?" በማለት የማንነት ማጣሪያ ጥያቄ ጠየቀው። "ማን እንደሆንኩና ከየት እንደመጣሁ ሌላ ጊዜ እነግርሃለሁ" በማለት የማንነቱን ጥያቄ በቀጠሮ በማለፍ ያ የሚያምር ቀይ ልብስ የለበሰ እንደጥጥ ነጭ በሆኑ ባዶ እግሮቹ የሚሄድ አዲሱ ወዳጁ በየጊዜው ወደሱ መምጣቱን ቀጠለ። በሚመጣበት ጊዜ ወደ ልጁ ሲገዘ ሳየው በድንገት ከሩቅ ሳይሆን ከቅርበት በአጠገቡ ይቆማል። ሲሄድ አብሮት ይሄዳል። ሲቀመጥ አብሮት ይቀመጣል። አብረው ይውሉና ማታ በጎቹን ጉረኖ አስገብቶለት ይለየዋል። ስሙን ስላልነገረው "እወድህለሁ" በማለት ደጋግሞ ስለተናገረው "እወድሃለሁ" እያለ ይጠረዋል። በጎች ሲሄዱበት "እወድሃለሁ እባክህ መልስልኝ" ሲለው ሄዶ እየነዳ ያመጣለታል። በዚህ አይነት ገርበሴና "እወድሃለሁ" አብረው ተግባብተው መዋል ጀመሩ።





ገርበሴ ጧት በጎቹን ይዞ መስክ ሲደርስ "እወድሃለሁ" የት አድሮ ይሆን ወንዝ ወይስ ዛፍ ላይ በማለት ወዲያ ወዲህ እየማተረ ይፈልገዋል። "እወድሃለሁ የት ነህ" ብሎ ሲጠራው አፍታም ሳይቆይ አጠገቡ ያገኘዋል። አብረው ይውላሉ። እንደውም አብረውም ከመዋል አልፈው ሌሊት በህልም ያነጋግረዋል። አንድ ጊዜ በሌሊት ህልም የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጠየቀው። "ጉንዳኖችን ማን ፈጠራቸው? በስርዓት እየሰሩ እንዲኖሩስ ማን አስማራቸው? ሁለቱ እግሮችህ በየተራ እንዲራመዱ ሁለቱ እጆችህ ተረዳድተው እንዲሰሩ ሁለቱ አይኖችህ እንዲያዩ ያደረገ ማነው? ይህንን እንቆቅልሽ የፈጠረውና ለአንተ የሰጠህስ ማነው? በማለት ቀድሞ ስለተፈጥሮ አስደናቂነት ገርበሴ ራሱ የሚጠይቃቸውን ጥያቄዎች አይነት መልስ ፈላጊ ብዙ ጥያቄዎችን ጠየቀው። ትንሹ ልጅ "እኔ አላውቅም" በማለት መለሰ። "ማለዳ ስትነሳ አባትህንና እናትህን ጠይቀህ መልሱን እንድታመጣልኝ" በማለት የቤት ሥራ ይዞ ከእንቅልፉ ይነቃል። ሌሊት በህልም የተሰጡትን ጥያቄዎች ጧት እናትና አባቱ ቡና ላይ እያሉ ጠየቃቸው። "እነዚህን ሁሉ ማን ፈጠራቸው?" በማለት። "እግዚአብሔር ነው የፈጠራቸው" ሲሉ በአጭሩ መለሱለት። "ቢሆንም አንተ ገና ልጅ ነህ ምን አስቸገረህ ትደርስበታለህ ቁርስህን በልተህ በጎቹን አሰማራ" በማለት ኤሊ ሳሙኤልን ከእግዚአብሔር ጋር እዳስተዋወቀው ሁሉ የሰማይና የምድር በውስጣቸውም ያሉ ፍጥረታት ፈጣሪ እግዚአብሔር መሆኑን ቀጥተኛና ወጥ የሆነ ግንዛቤ እንዲያገኝ አደረጉት።

"ሳሙኤል ግን ገና እግዚአብሔርን አላወቀም ነበር የእግዚአብሔር ቃል ገና አልተገለጠለትም ነበር፤ እግዚአብሔርም ሳሙኤልን እንደገና ሶስተኛ ጊዜ ጠራው እርሱም ተነስቶ ወደ ኤሊ ሄደና እነሆኝ የጠራኸኝ አለ። ኤሊም ሳሙኤልን ሄደህ ተኛ ቢጠራህም አቤቱ ባሪያህ ይሰማልና ተናገር በለው አለው። ሳሙኤልም ሄዶ በስፍራው ተኛ። እግዚአብሔርም መጥቶ ቆመ እንደቀድሞውም ሳሙኤል ሳሙኤል ብሎ ጠራው። ሳሙኤልም ባሪያህ ይሰማልና ተናገር አለ" (1ሳሙኤል 3:7-10)

በማግስቱ "እወድሃለሁ" ስለ ፍጥረት ፈጣሪ ጠይቅ ብሎት የነበረውን ጥያቄ ሲገናኙ "ማን ፈጠራቸው አሉህ" ሲል ጠየቀው። "የፈጠራቸው እግዚአብሔር ነው አሉኝ" በማለት መለሰለት። እርሱም "ትክክል ነው የፈጠረውና ያደረገው እግዚአብሔር ነው" በማለት አረጋገጠለት።

"ከእግዚአብሔር በቀር አምላክ ማነው ከአምላካችንስ በቀር አምላክ ማነው?" (መዝሙር 18:31)

ገርቦሌ የእግዚአብሔርን ፈጣሪነት ካወቀ ጊዜ ጀምሮ "እግዚአብሔርን ወደድኩት በጆሮየም እግዚአብሔር እግዚአብሔር ነው የሚል ድምፅ እሰማ ጀመር" በማለት እግዚአብሔርን ያወቀበትን ያንን ሁኔታ በማስታወስ ይናገራል። "የምወደውን ያንን ሰውና እግዚአብሔርን ልዩነት በሌለው ሁኔታና በአንድነት በልቤ አገኘኋቸው" በማለት እግዚአብሔር በአካል የተገናኘው ያ ሰው ትዝታውን ያጫውተናል። በዚህ አይነት አሁን ማንነቱን የተረዳው





የገርቦሌ ወዳጅ አንድ አመት ያህል በሚዳ በወንዝ በቤት በቀንና በሌሊት በሄደበት ሁሉ እያስተማረው እየመከረውና እየረዳው አሳለፈ። ይህ ልጅ "ከሚወደው" ጋር ሲነጋገር የሚያናግረውን የሚያየው እሱ ብቻ ነው የገርቦሌ ድምፅ ብቻ ነው ለሚመለከት ሰው የሚሰማው። ከዚህም የተነሳ ገርቦሌ ብቻውን ያወራል ይባል ጀመር። ልጁ ጤናው እንደተቃወሰ ከዚህም የተነሳ ብቻውን እንደሚያወራ ቤተሰብና አካባቢው ሁሉ የተማመነበት ጉዳይ ሆነ። የሚያወራው ብቻውን ካልሆነ ሊሆን የሚችለው ከአድባር ጋር መነጋገር ነው አድባር እያነጋገረው ሊሆን ይችላል። ይኼ ሁለተኛው ግምት ነው። በጉዳዩ እጅግ የተጨነቁት አባትና እናቱ እንደሊላው አውርተው ማለፍ አልቻሉም። ልጃቸው ከማን ጋር እንደሚነጋገር መከታተልና ማጣራት አስፈላጊ ሆኖ ስላገኙት ይህንን ሀላፊነት ለሚያምኑት ለታላቁ ልጃቸው በመስጠት አብሮት ወደ መስክ እንዲወጣና በግልፅም በስውርም ክትትል በማድረግ ልጃቸውን የሚያነጋግረውን አካል እጅ ከፍንጅ ለማግኘት መረጃ ይዞ እንዲመለስ ላኩት።

የተመደበው አጣሪ ሙሉ ቀን በንቃት ሲከታተል ዋለ። ታናሽ ወንድሙ ግን ከማይታይ አነጋገሪ ጋር እንደተለመደው ተረጋግቶ ያወጋል። በርቀትም በቅርበትም የተገለጠ ወይ በቁጥቋጠ ውስጥ የተደበቀ ከሆነ በማለት ቢፈልግ ሊያገኝ አልቻለም። ስለዚህ ማታ ሪፖርቱን ይዞ ወደላኩት ወላጆቹ ሲገባ "እኔ ምንም አላየሁም ልጁ የሚያወራው ብቻውን ነው" በማለት አጭርና ግልፅ ዘገባ አቀረበ።

ብቻውን ያወራል የሚለው የጥናት ውጤት ይፋ ከሆነ በኋላ ልጃችን ታሟል ተብሎ መላው ቤተሰብ ድምዳሜ ላይ ደረሰ፡፡ ከዚህ በኋላ ለልጁ ከማዘን የተነሳ አጉል ቦታ ወድቆ ይቀራል በማለት ጥበቃ ይደረግለት ጀመር፡፡ እንደቀድሞው ሩቅ ቦታ እንዳይላክ ወንዝ ለብቻው እንዳይሄድ በጎች በሚጠብቅበትም የቤተሰብ አይን ሳይርቀው አልፎ አልፎ ብቅ እያሉ የበጎቹ ጠባቂ ተደራቢ ጥበቃ እንዲደረግለት ሆነ፡፡ ራሱን ችሎ በጤና እንደሚንቀሳቀስና እንደሚሰራ ሰው መታየቱ ቀረ፡፡

ይህ በእንዲህ እያለ በሆሮ ጉድሩ "አሙሩ ከተማ ላይ እግዚአብሔር ወርዷል" የሚል ወሬ ወደ ኢቡንቱ መጣ፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፡፡ በ1950ዎቹ አጋማሽ ገደማ የውጭ አገር ሚሲዮናውያን ወደዚያ አካባቢ በመሄድ በከተማዋ ውስጥ የህክምና አገልግሎት እየሰጡ ወንጌል መስበክ ይጀምራሉ፡፡ ይሁን እንጂ ቋንቋና ባህል በነሱና በተደራሹ ሕዝብ መሀል ግድግዳ ይሆንባቸውና ውጤቱ የተጠበቀውን ያህል ሳይሆን ይቀራል፡፡ ሆኖም በዚያ ምድር ላይ እግዚአብሔር ሊሠራው ያቀደው ነገር ነበርና ሀገርኛ አማኞች በመምህርነት ወደዚያ ተመድበው ሄደው ስለነበር በአሙሩና በአካባቢው ወንጌልን በመስበክ ለታመሙ በመፀለይ ድንቅና ተዓምር ይሆን ጀመር፡፡ አጋንንት ያለባቸው ገና በሩቁ እየጮኹ ይወጣላቸዋል፡፡ ለብዙ ዘመን የተጨነቀ ሕዝብ ነበርና ለብዙ በሽታና ችግር አንዱ ለአንዱ ያገኘውን የመፍትሔ ዜና የዛምተው ጀመር፡፡

"የዛብሎን ምድርና የንፍታሌም ምድር የባህር መንገድ





በዮርዳኖስ ማዶ የአህዛብ ገሊላ በጨለማ የተቀመጠው ሕዝብ ታላቅ ብርሃን አየ በሞት አገርና ጥላ ለተቀመጡትም ብርሃን ወጣላቸው" (ማቴዎስ 4:14-16)

እንደተባለ ሁሉ የሆሮ ጉድሩ የአሙሩ ምድር ከአባይ ማዶ ያለው አገር በጨለማ የተቀመጠው ህዝብ ታላቅ ብርሃን አየ ሆነ ማለት ነው፡፡ ይህ የታላቅ ብርሃን መውጣት የምስራች እስከ ኢቡንቱ ወረዳ ሆሮጬ ቀበሌ እስከነ ገርቦሌ ሰፈር ብሎም እስከ ቤታቸው ድረስ መጣ፡፡ ያን ጊዜ ሰው በየቤቱ ያለውን በሽተኛ እያጓጓዘ ሊላውም ሁኔታውን ለማየት ስንቅ እየቋጠረ የሁለትና የሦስት ቀን መንገድ ተጉዞ ታዓምር የሚታይበት አሙሩ ይደርሳል፡፡ በዚያ ወንጌልን እየሰበኩ ለበሽተኞች የሚፀልዩ እነመምህር መኩሪያ፣ ሙሉጌታና ባልንጀሮቻቸው ይገኛሉ፡፡ በነገርቦሌም ቤት ወሬው ሲሰማ በቤታቸው ያለው ችግር መፍትሄ ተገኘለት ብለው አሰቡ፡፡ በሽተኛ ልጃችን መድሀኒት ከተገኘ አሁንም ያው ታላቅ ወንድም ሄዶ ይዞ እንዲያመጣለት ተባለና ተላከ፡፡ ሰነባብቶ ሲመጣ ግን እንደጠበቁት የሚጠጣ ወይ የሚቀባ መድሃኒት ይዞ አልነበረም የመጣው፡፡ ለታመመው ልጃቸው ያገኘውና ይዞት የመጣው ራሱ ተለውጦና አንድ አዲስ መፅሐፍ ቅዱስ ይዞ ነበር የመጣው፡፡

አሙሩ ላይ ለዚህ ሰው የገጠመው ነገር ወንጌልን መስማት የሰማውን ማመንና ንስሀ ገብቶ የአቋም ለውጥ ማድረግ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝነት ማወቅ ነው፡፡ በጌታ አምኖ ተመለሰ፡፡ እንደመጣ ያደረገው ነገር ቤተሰቡን ሰብስቦ "ሰይጣንን እንካድ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እንመን በቤታችን ያለውን የሰይጣን መሰዊያ

እናፍርስ ለአድባርና ለዛፍ ለጨሌ መስዋት ማቅረብ እናቁም በማለት በቤት ውስጥ የነበረውን መሰዊያ ነቃቅሎና አፈራርሶ ወደ ደጅ ጣለው፡፡ በዚያ ዘመን በዚያ አገር በየሰዉ ቤት ውስጥ እንደ አልጋ ወይም እንደመደብ የሚሰራ የአጋንንት መሰዊያ ነበር፡፡ ሰዎቹ ምግብ ሲያበስሉም ሆነ ቡና ሲያፈሉ ወይም ካለቡት ወተት ላይ ከመጠቀማቸው በፊት ለመናፍስቱ በዚያ መሰዊያ ላይ ያስቀምጡ ነበር፡፡ ወደ አሙሩ ሄደው እግዚአብሔር የሚሰራውን ተዐምር ያዩና ወንጌልን የሰሙ ወደየቤታቸው በመምጣት ይህንን የጎጃ ማምለኪያቸውን አፈራርሰዋል፡፡ የገርቦሌም ወንድም ያደረገው ነገር ቢኖር ይህንኑ ነው፡፡

በተጨማሪም ማንበብ አይችልም እንጂ ያመጣውን አዲስ መጽሐፍ ቅዱስ ከፍቶ እግዚአብሔርን ፍሩ ከሰይጣን ተመለሱ በማለት በአንድ እግሩ በመቆም "ኢየሱስ አድነኝ ልጅህ አድርገኝ" እያለ እጆቹን ወደ ሰማይ በመዘርጋት ይፀልይ ነበር፡፡ ከዚህም ባለፈ ኢየሱስ ያድናል እያለ ወንጌልን እየመሰከረ ለአካባቢው ሕዝብ ይናገር ነበር፡፡ ገርቦሌም ከወንድሙ ጋር ኢየሱስ ያድናል ማለትም ማመንም ጀመረ፡፡ ቀደም ሲል እግዚአብሔር በግል ቢገናኘውም መልክ ባለው ሁኔታ የሚያምነውን ዕውቀት አገኘ፡፡ ለጊዜውም ቢሆን ገርቦሌና መፍትሔ አፈላላጊው ታላቅ ወንድሙ "በሽታቸው አንድ አይነት ሆነ" ተባለ፡፡ ታላቅ ወንድሙ ወንጌልን ከነገረው በኋላ ቀደም ሲል በቀንና በሌሊት ያነጋግረው የነበረው ተገልጦ እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ነገረው፡፡ "እኔ ላድንህ የመጣሁ ስለ አንተ መከራን የተቀበልኩ ሞቼ የነበርና የተነሳሁ የሞትና የሲኦል ቁልፍ ያለኝ





በክብር የምመለስ ጌታ ነኝ አለኝ" ይላል ገርቦሌ፡፡ ስለዚህ ሁኔታ ሲያወራ፡፡

ተከታታይ መንፈሳዊ አገልግሎት ማግኘት ያልቻለው የገርቦሌ ታላቅ ወንድም በውስጡ ተጭሮ የነበረውን እሳት የሚቆሰቁስለትና የሚያነደው በማጣቱ ያንድ ክብሪት እንጨት ያህል ነዶ ወዲያው ጠፋ፡፡ ማንበብ አለመቻሉም ራሱን በራሱ እያከመ ለማቆየት ሳያስችለው ቀረ፡፡ ስለዚህ ቀስበቀስ እየቀዘቀዘ መጥቶ የጌታን ስም መጥራት እስከመተው ደረሰ፡፡ አንዱን ሲያነሱ አንዱን መጣል አንዱን ሲጥሉ ሌላውን ማንሳት የማይቀር ነውና ጌታን ሲተው ወደተወው የቀድሞ እምነቱ ተመለሰ፡፡ ያፈረሰውን የቤት ውስጥ መሰዊያ በጠራራ ፀሐይ እንደነበር መልሶ ሰራ አጋንንታዊ አምልኮውንም ቀጠለ፡፡ ከእንግዲህ ወዲህ የኢየሱስ ነገር ለገርቦሌ ተትቷል፡፡ ድሮም ቢሆን የሄደው መድኃኒት ሊያመጣለት ነው፡፡ አገልግሎቱን ማለትም መድኃኒት ለወንድሙ ማምጣቱን ተወጥቶታል ኢየሱስ ያድናልን አምጥቶለታል፡፡ ራሱም ድኖ ቢቀር መልካም ነበር፡፡ በበፊቱ "ያመዋል" ላይ "ኢየሱስ ያድናል" ተጨምሮ ለገርቦሌ ቤተሰብ ከበፊቱ የባሰ ምቾትና ሰላም የሚነሳ ነገር ሆኖባቸዋል፡፡ ማስተው እንዳለባቸው ወሰኑ፡፡ የማስተው ሂደቱን ለመፈፀም የተመረጡት እናቱ ናቸው፡፡

ከእለታት አንድ ቀን ከረሜላና የዝሆን ምልክት ያለበት ትንሽ የወንጂ ስኳር ከረጢት ሰጥተውት "ና ልጄ ዘመድ እንጠይቃለን" በማለት ትንሹን ልጅ አስከትለው እሳቸው ፊት ፊት ገርቦሌ

እየተከተለ ከቤታቸው ወጥተው ቀጭኗን መንገድ ይዘው ወደ ትልቁ ጎዳና ከገቡ በኋላ ወደ ፊት ገሰገሱ:: በመንገድ ሳሉ "ልጄ" አሉ እናት "እመት" አለ ልጅ "የምንሄድበት ቦታ ያ የምትጠራው ስም ስለማይፈለግ እዚያ እንዳትጠራ ከፈለክ አሁን በመንገድ እያለን ጠርተህ ጠርተህ ይውጣልህና አቁም" አሉ እናት:: የሄዱት ዘመድ ጥየቃ ሳይሆን ጠንቋዩዋ ወለቴ ቤት ነበር:: ወለቴ ቤት እንደደረሱ እናት የተለመደውን የቃልቻ ቤት ስርዓት ከፈፀሙ በኋላ የመጡበትን ተናገሩ "ልጄ ያመዋል ሲሊትና ቀን ዕረፍት የለውም ብቻውን ያወራል ስለወደፊቱም ፈራሁ ወጥቶ የሚገባ አይመስለኝም፣ ይኼ ልጅ ያድጋል ወይስ ይሞታል? ቁርጡን ማወቅ እፈልጋለሁ" በማለት በልመናና በተማፅኖ ተደፍተው አለቀሱ::

ወለቴ ሥራዋን ቀጠለች ቡና ተቆላና የልጁ የእጅ መዳፍ ተነበበ:: ውጤቱንም ለእናት እንዲህ በማለት ጀመረች "እንዲህና እንዲያ አድርገሽ ሞክሪ" "ልጄ ምን ይሆናል" በማለት እናት በከፍተኛ ድንጋጤና እንባ ጠየቁ:: እናቱ እየተርበተበቱ ሲያለቅሱ ማየት ገርቦሌን አስደነገጠው "ጌታ ኢየሱስ ይቺን ሴት ያዛት እናቴን አስደንግጣለች እባክህ ያዝልኝ" ገና ከማለቱ ወለቴ ቃልቻዋ እሪታዋን አቀለጠችና ወደቀች:: ሰፈሩ በጩኸቷ ታመሰ ሁሉም ነገር ዝብርቅርቁ ወጣ:: ወለቴን ኢየሱስ ስለማለት ገርቦሌ በጣም ፈነደቀና በአካባቢው አባባል ለጎበዝና ለብርቱ የሚባለውን አባባል በመጠቀም "ኢየሱስ ወንድ ነህ" አለ:: "ልጄ ጉድ ሰራኸኝ ይህንን ስም እዚያ ቦታ አትጥራ አላልኩህም" አሉት የመልስ መንገዳቸውን እየጀመሩ:: "እናቴ እኔ ምን ላድርግ መጣብኝና ተናገርኩ":: ከዚያ





በኋላ ወደ ሌላ ጠንቋይ አልወሰዱትም::

ይሁን እንጂ ወለቴ እንዲህ እና እንዲያ ቢደረግለት ይለቀው ይሆናል ብላ መጀመሪያ በሚስጥር ለእናቱ የተነገረው መፍትሄ መሞከር ነበረበት:: ይኸውም ማለዳ ወፍ ሲንጫጫ ሰው ወንዝ ሳይሻገር ውሃው ሳይቀዳ ሰውና ሰው መተያየት ሳይጀምር ጥቁር ዶሮና ቢላ ይዞ ወደ ወንዝ መውረድና በፏፏቴው ዳር አርዶ መጣል ፊቱን አዙሮ ሳይገላመጥ በመጣበት መንገድ መመለስ ነበር:: እንደተባለው ለመፈፀም እናት ዶሮ ገዝተው ስለአፈፃፀሙ ትክክለኛነት አመራር ለመስጠት ሲነጋጋ ተቀስቀሶ እናት ገርቦሌን እቅፍ አድርገው እንዲህ አሉት:: "ልጄ እህትህ እንደምትልህ አድርግ ቆንጆ ቦቲ ጫማ ልብስና የምትለኝን ሁሉ እሰጥሃለሁ" ሰማለት ሸኟቸው:: ዶሮና ቢላዉን ባለጉዳዩ ተሸክሞ እህት እየመራች ወንዝ ደረሱ::

ትክክለኛ ቦታውን ካሳየችው በኋላ "በል ቶሎ እረድና እዚያ ጋ ጥለህ ፊትህን አዙረህ ተከተለኝ" በማለት በፍርሃትና በብርድ እየተንቀጠቀጠች አመራር አወረደችለትና እሷ በጀርዋ ብቻ ትከታተል ጀመር:: መስዋዕት አቅራቢው እንደሚፈለገው አልፈጠነም:: "ቶሎ በል ቆርጠህ ጣል" በማለት ድጋሚ ተቆጣች:: የዶሮውን አንገት ከቆረጠ በኋላ ዝም ብሎ ገደል ጫፍ መጣሉ አልተዋጠለትም ትርጉምም አልሰጠውም:: "የሚቀበለኝ መኖር አለበት ለማን ነው የምሰጠው የት አለ ባለዶሮው" ብሎ እህቱን መልሶ ጠየቀ:: "አርደህ ጣልና ተከተለኝ" አሁንም ቁጣ:: የዶሮውን አንገት ቆረጠው:: ዶሮው ሲርገፈገፍና ሲንደፋደፍ ስትሰማ "ቦታ

ተከተለኝ" ብላ መንገድ ገባች፡፡ ወደኋላ ማየት ስለሌለ ሁለቱም ፊትና ኋላ እንደጋሪ ፈረስ በፍጥነት እየተራመዱ ግቢያቸው ደረሱ፡፡

አሁን ልጁ "ይድናል" ብሎ በተስፋ የሚጠብቀው ቤተሰብ ደጅ ተሰብስቦ ተቀበላቸው፡፡ "እሪ" አሉ እናት ወደቁ መሬት ተንከባለሉ" "አበስገበርኩ አውጣን ይቅር በለን ጣጣውን እንደያዘ እሱኑ እዛው ጠይቀው" በማለት ሣር እየበጠሱ ወደ ሰማይ በተኑ፡፡ ለካስ ገርበሌ ዶሮውን ቢያርድም ፏፏቴው ላይ እንደተባለው አልጣለውም፡፡ የሚቀበለኝ አጣሁ በማለት የሞተውን ዶሮ ትከሻው ላይ ጥሎ ልብሱ ደም በደም ሆኖ መስዋዕቱን ይዞ ከመምጣቱም ባለፈ ሰይጣኑን ወንዝ ድረስ ሄዶ በማጓጓት ሳይሰጠው በመመለሱ የአፀፋውን በትር ከኛ አርቅ እኛ ያንተው ተገዢ ነን የመፀብሀን ጠይቅ ነበር እዝነታው፡፡ "ነይ አንቺ ግቢ" ተባለች እህቱ ለብቻው በብርድ የሚንቀጠቀጠው ገርበሌ ከሰው እንዳይደባለቅ ተነገረው "ሂድና የያዝከውን ዶሮና ልብስህን ወደ ሸለቆ ጣል" ተባለ፡፡

እንግዲህ ከዚህ በኋላ ነው የእናቱ የአደኤ ተረፈች ልብ በሀዘንና በተስፋ መቁረጥ የተሰበረው፡፡ እንደሚሞት እርግጠኛ ሆኑ እግዚአብሔር እንደሚያድን ባይረዱም እንኳ ሰይጣን እንደሚገድል በደንብ ያውቃሉ፡፡ ብዙም ዕድሜ ስለሌለው ተብሎ ሥራ ተቀንሰለት ደስ የሚያሰኘው ይደረግለት በማለት ሱቅ ነበራቸውና ከሱቃቸው ልብስና አዲስ የመጣች ቦቲ ጫማ ተሰጠው፡፡ ለልጁ ተመችው ውስጡ ሰላም ወጪው አዲስ በአዲስ ግን ሰው ደስታውን አላወቀለትም፡፡





ያም ሆኖ አባቱ ቅዳሜ ቅዳሜ ገበያ እየወጡ ጨው ይነግዱ ስለነበር ወደ ገበያ ሲወጡ "ልጄ ገድህ ጥሩ ስለሆነ እንዲቀናኝ በትሬን ስጠኝ" ይሉታል ቀንቷቸው ይመለሳሉ፡፡ እናቱም እንዲሁ "የኔም ገበያ እንዲቀናኝ ኮንጥላዬን አቀብለኝ" ይላሉ በፋንታቸው፡፡ የታመመ ሰውም ወደ ቤታቸው ያመጡና "እስቲ በእጅህ ንካው" ሲነካው ይድናል፡፡ ከብቶች የታመሙባቸው ወይ አልታለብ ያለች ላም አልጠመድ ያለ በሬ የገርበሌን እጅ ያስነካሉ ሁኔታው ይለወጣል፡፡ አቦ ሂርጳ ለዚህ ልጅ የተለየ ፍቅር ነበራቸው፡፡ ልጃቸውም ሚስጥረኛቸውም ነበር፡፡ ከመሞታቸው በፊት ታመው በተኙበት አልጋ ላይ ሆነው "ገርበሌ" አሉት "አቤት" "ጨው አምጣልኝ" አሉት ከሚሸጠው አሞሌ አንዱን አንስቶ አቀረበላቸው "ላሰው" አሉት፡፡ ላሰው፡፡ "እንደዚህ ጨው ጣፍጥ ለማጣፈጫ ሁን ልጄ" ብለው መረቁት፡፡

# ጌታን ማወቅ

ትንሹ ገርቦሌ ወንዝ ዳር ዶሮ አርዶ ትከሻው ላይ ተሸክሞ ከተመለሰም በኋላ በጤናው ላይ የሆነ ችግር እየተፈጠረ እንደሆነ በየቀኑ እየገባው መጥቷል፡፡ ያመዋል፡፡ በትከሻው ከባድ ሸክም ተጭኖበታል ሸክሙ ለሰው አይታይም ለሱ ይታየዋል ቀንም ሌሊትም ከትከሻው የማይወርድ በትልቅ ማዳበሪያ የተሞላ አሸዋ የተሸከመ ይመስለዋል፡፡ ለዚህ ማስረጃው የተሸከመበት ትከሻው በሸክሙ ቆስሏል፡፡ ከክብደቱም የተነሳ ሁሌ በጣም ይደክመዋል፡፡ የድካም ስሜት ይሰማዋል እንደልቡ መተንፈስ መንቀሳቀስ አይችልም፡፡ ልቡ ወደታች ስልብ ይላል፡፡ የልብ ድካም ይዞታል ይላል ሰው፡፡ ከድካሙ የተነሳ ይተኛል፡፡ አሁን ያልጋ ቁራኛ ሆኗል፡፡

ታላቅ እህቱ አበዙ በትዳር ዳረጎስ የሚባል ቀበሌ ሄዳ ትኖር ነበር፡፡ ቤተሰቦቿን ለመጠየቅ ስትመጣ ያ"ጣጣ የማያጣው ልጅ ምን ሆነ" ብላ ጠየቀች "የልብ ድካም ያዘው" ሲሉ መለሱላት፡፡ አበዙ ትንሽ ካጠጣች ካወረደች በኋላ "ይኼ ልጅ እኛ አካባቢ በሽተኞች የሚድኑበት ፀሎት ቤት አለና እዚያ ቢሄድ ይድናል አለበለዚያ ግን እዚህ ተኝቶ መሞቱ ነው" ስትል የማታምነው ሰው በማመን ስለሚዳንበት ሁኔታ ለቤተሰቡ ሰበከች፡፡ ከቤተሰቡ አንዳንዱ እዛ ከሄደከ መዳን ብቻ አይደለም ሀይማኖቱንም ይለውጣል በማለት ጉም ጉም አሉ፡፡ እናት ግን ልጄ ይዳን እንጂ የፈለገውን ሀይማኖት ይከተል በማለት የመጨረሻውንና ወሳኝ ስልጣናቸውን በመጠቀም





ታማሚው ልጅ ወደተኛበት ጥግ "ኑ ያዙ ተሸከሙት" በማለት የወንዶቹን ርዳታ ጠየቁ፡፡ ካሁን አሁን ይሞታል ተብሎ ይጠበቅ ስለነበር ዘመድና ጎረቤት ብዙም ርቆ አይሄድም፡፡ ሩቅ ያለችው አበዙ እንኳ ይኼው ስጋት ነው ያመጣት ለሽፋን ግን "ቤተሰቤን ልጠይቅ" ብላ መጣች፡፡ ልጁ እንዴ ትንፋሹ ይጠፋል እንዴ ይመለሳል ይኑር ይሙት አይታወቅም፡፡ ለይቶለት ቀብረው ቢያርፉ ውስጥ ውስጡን የሚመኙም ነበሩ፡፡ ችግሩን ለመጋፈጥ ወደኋላ የማይሉ ሦስት ያህል ወንዶች ወደተኛበት መደብ ተጠጉ፡፡ ከልጁ ይልቅ እላዩ የተቆለለው ጨርቅ ይበልጣል አንዳንዴ እያንጠረጠረ ያንዘፈዝፈዋልና፡፡ ገለጥለጥ አደረጉት አካሉ ሰልስሏል፡፡

ወ/ሮ ሴቀታ ገለታ የዳርጎስ ፀሎት ቤት አገልጋይና መሪ ነው፡፡ ለዚህ በሸክም ለመጣው በሽተኛ ልጅ ፀለዩለት፡፡ በዚሁ ቅፅበት ገርቦሌ ስለተደረገለት ፈውስ ሲናገር "ለኔ ብቻ የሚታየኝና ትከሻዬን ያጎበጠው ሸክም ከላዬ ወደቀ፡፡ ሞት ከላዬ ላይ ተገፎ ሄደ፡፡ ከልቤ ጀምሮ የሚሰማኝ ሕመምና ድካም ሁሉ እንደልብስ ከላዬ ላይ ወለቀ፡፡ ተራገፈልኝ፡፡ ሰላምና ጤንነት ተሞላሁ፡፡"

ለተወሰነ ጊዜ በደንብ እስኪሻለውና ሰውነቱ በርትቶ በደንብ በእግሩ ቆሞ መሄድ እስከሚችል እዚያው ፀሎት ቤት ይቆይ ስለተባለ የመጡት ወደ ቤታቸው ሲመለሱ እሱ እዚያው ቀረ፡፡ የከዚህ በፊቱ የገርቦሌ መንፈሳዊ ልምምድ እግዚአብሔር የሁሉ ፈጣሪ መሆኑን ማወቁና ኋላም ታላቅ ወንድሙ ከሩቅ ሀገር ይዞት የመጣው ኢየሱስ ያድናል የሚለው የወንጌል ቃል ነው፡፡ በርግጥ የመንፈሳዊው ነገር ምሰሶ ይኸው ነው፡፡ ግን ዝርዝር ዕውነቱን ሰው

መማር አለበት፡፡ ገርቦሌ ታዲያ አንድም የመፅሐፍ ቅዱስ ቃል አልተነበበለትም ወይም የተረዳውን እውነት ለማሳደግ መንፈሳዊ ምግብ የመገበው ማንም የለም፡፡

"እኔ ተከልሁ አጵሎስም አጠጣ ነገር ግን እግዚአብሔር ያሳድግ ነበር" (1ቆሮንቶስ 3:6)

አንድ ሰው በወንጌል አምኖ እንዲለወጥና ሥር እንዲሰድ አስተዋፅዖአቸው የማይዘለል ተከታታይ አገልግሎቶች አሉ፡፡ ያትንሽ ልጅ ከአቅሙ በላይ የሆነ ዕውቀት ተሸክሞ ሊያቆመው የሚችል ተከታታይ አገልግሎት ባለማግኘቱ ከወዲያ ወዲህ ይላጋል፡፡ ወደ ጠንቋይ ቤት ወደ ወንዝ አሁን ደግሞ ወደ ፀሎት ቤት ይኼኛው መልካም ነው፡፡ የዳረጎስ ፀሎት ቤት ቆይታው ወርቃማ አጋጣሚ በመሆኑ ቀድሞ ያላገኛቸውን መንፈሳዊ አገልግሎቶች ማግኘት አስቻለው፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል መስማት መንፈሳዊ ዝማሬዎችን መስማትና መዘመር ከደረቅ መሬት ወደ መኖሪያው እንደገባ አሳ ገርቦሌም በዚህ መንፈሳዊ በረከት ውስጥ ይዋኝ ጀመር፡፡ ከውስጡ ጋር ተደማምጠና ተስማምቶ "እኔም እንደ ወ/ዊ ሴቀታ ገሊታ መሆን እንዳለብኝ የወሰንኩት ያኔ ነው" ይላል ገርቦሌ ስለ አገልጋይነት ውሳኔ ጅማሬ ሲናገር፡፡

ሙሉ ለሙሉ ድኖ መንፈሳዊውን በረከት ተመግቦ ወደ ዳረጎስ በሸክም የሄደው ልጅ እየዘመረና እየቦረቀ ወደ ቤቱ ተመለሰ፡፡ ከዚያም በኋላ አልፎ አልፎ ወደዚያች ፀሎት ቤት በመሄድ ያመልክና ከወገኖች ጋርም ይገናኝ ነበር፡፡ "ከወገኖች ጋር





ስደባለቅ ጌታን በአካል ማየቴ አቆመ ከዚህ ሁኔታ በኋላ ድምፁን በመስማት ብቻ ተወሰንኩ" በማለት ከወገኖች ጋር ያለው ኅብረት ስላለው ታላቅ ዋጋ ማለትም ከወገኖች ጋር መሆን ከጌታ ጋር ከመሆን ጋር መተካከሉን ሁለትና ሶስት ሆነን ባለንበት ጌታ ከኛ ጋር በዚያ የመኖሩን ተስፋ የሚያጠብቅ ዕውነት ያስጨብጠናል፡፡

ጌታ ለመጨረሻ በአካል የተገለጠለትን ጊዜና ሁኔታ ሲያስታውስ ገርቦሌ እንዲህ በማለት ነው፡፡ "አትሞትም በህይወት ትኖራለህ እምነትና ፍቅር ቅንነትና ትህትና ምህረትና ልግስና ትዕግስትና ፅናት የተባሉትን የቃል ኪዳን መዛግብት ሰጠሁህ ብሎ እንደሚዳሊያ በአንገቴ አጠለቀልኝና እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ሰው ሁሉ ባንተ ላይ ይኼንን እንዲያነብና እንዲጠቀም አንተም የዚህ መዝገብ አገልጋይ እንድትሆን ሾምኩህ" አለኝና ሄደ፡፡ ከዚያ ወዲያ በድምፁ ወደኔ ይመጣል እንጂ በአካል አላየውም፡፡ በአንፃሩም ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ሕይወቴም ተለወጠ፡፡ ጌታንም ተለማመድኩ ዕምነቴም ሥር መስደድ ጀመረ፡፡"

ገርቦሌ በትክክል ጌታን ተቀበልኩ ብሎ የሚያስበው በ1966 ዓ.ም ነው፡፡ በ1967 ዓ.ም ማንበብ ባይችልም በሠላሳ ሰንቲም መፅሐፍ ቅዱስ ገዛ፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ስለሆነ ይወደዋል አይለየውም ቀድሞ እወድሀለሁ የሚለውን ወዳጁን ይህ መፅሐፍ ቅዱስ ተካልኝ ይላል፡ የታመሙ ሰዎችን በመፅሐፍ ቅዱሱ ሲነካ ይፈወሳሉ፡፡ አጋንንት ይጮሀሉ ይወጣሉ፡፡ የፈውሱ ጉዳይ እናቱን እንኳ በማስገረም አስቀንቷቸዋል፡፡ የበሽታና የጤና ጉዳይ አለም ከወደቀች ጊዜ ጀምሮ የሰው ሁሉ አጀንዳ ነውና "እባክህ ልጄ

እንጨት ብጤ ቆርጠህ ስጠኝ ሲያመኝ የገርቦሌ አምላክ ብዬ ስነካው እንድፈወስ" በማለት ጠየቁት፡፡ ገርቦሌ "እልሰጥሽም የፈውሱን ጌታ ኢየሱስን ከፈለግሽ ተቀበይና የህይወትሽ ጌታ አድርጊው" ቢላቸውም ጌታን የተቀበሉት ብዙ አመት ቆይተው ነው፡፡

ቀስ በቀስ ቤተሰቦቹም አካባቢውም እየጠላው መጣ፡፡ መልካም እያደረገ ሲታመሙ እየፀለየ ሲልኩት እየተላከ ሲያዙት እየሰራ ጠሉት፡፡

"ዓለም ቢጠላችሁ ከእናንተ በፊት እኔን እንደጠላኝ እወቁ ከአለምስ ብትሆኑ ዓለም የራሱ የሆነውን ይወድ ነበር ነገር ግን እኔ ከዓለም መረጥኋችሁ እንጂ ከዓለም ስላይደላችሁ ስለዚህ ዓለም ይጠላችኋል፡፡ ባሪያ ከጌታው አይበልጥም ብዬ የነገርኳችሁን ቃል አስቡ፡፡ እኔን አሳደውኝ እንደ ሆኑ እናንተን ደግሞ ያሳድዷችኋል፡፡ (ዮሐንስ 15፥18-20)

"አሁን ድነህል ወደ ፈለክበት ቦታ ሂድ ወይም ወደ መሰሎችህ ሂደህ ተደባልቀህ ኑር" በማለት ከቤት አስወጡት፡፡ በጊዜው ወደየት እንደሚሄድ ማሰብ አልቻለም፡፡ ቀደም ሲል የሚያውቀው የአውሬ መኖሪያ ዋሻ ለጊዜው ታወሰው መጠለያ ነው፡፡

ደጋጉሌ ወደሚባለው ጫካ ውስጥ የሚገኝ ዋሻ ከርከሮ፣ አሳማና የመሳሰሉት አውሬዎች የሚኖሩበት ጫካ ሲሆን ወደ ዋሻው የምታስገባ በር አለች በዚያ ሲገባ እንደጠረጴዛ ጠፍጣፋ አለት ይገኛል፡፡ ገርቦሌ ወደ ዋሻው ሾልኮ በመግባት እዚህ አለት ላይ ተጋድሞ ያድራል፡፡ አልፎ አልፎም በጫካው ውስጥ በመደበቅ





ይኖራል ይፀልያል፡፡ የታላቅ ወንድሙ የደባለኝ ባለቤት ቀነኒ ገርቦሌን በጣም ትወደዋለች ታዝንለታለችም፡፡ "ምግብ እየሰራሁ ቀፎዎቹ መሀል ያለው ባዶ ቀፎ ውስጥ አደርግልሀለሁ ከዚያ እየወሰድክ ብላ" ብላው ስለነበር በጨለማ ወደ ቀፎዎቹ መሀል ገብቶ ከባዶው ቀፎ ውስጥ ያስቀመጠችለትን ይወስዳል፡፡ ሞገርና ደረጎስ ፀሎት ቤት ካልሄደ በቀን አንዴም ቢሆን በዚህ ዓይነት ምግብ ያገኛል፡፡ ኋላ ኋላ ትንሽ ወንድሙና እንዲት ውሻ ሚስጥሩን ስላወቁ ቀድሞ ካልወሰደው ይበሉበታል ስለዚህ ያች ምግብ ሦስት ተጠቃሚ ይጠብቃት ነበርና ከሦስቱ አንዱ የቀደመው ይመገባታል፡፡

# በቋጥኝ ላይ የበቀለች ዋርካ

በተደላደለ መሬት ላይ የበቀሉ ዋርካዎችን ያየሁት አርሲ ነጌሌ አካባቢ ነው፡፡ እነዚያ ዋርካዎች በሜዳ ላይ በቅለዋል ውሃ እንደልብ ያገኛሉ ሥራቸው አፈሩን ወደ ፈለገው አቅጣጫ እየሰረጎደ በምድር ውስጥ እንደ ሸረሪት ድር ተወሳስቧል፡፡ በተረፈ ግን እኔ በብዛት ያየኋቸው ዋርካዎች የበቀሉት በገደልና በፈፋ ላይ ተንጠልጥለው ነው፡፡ አንዲት የዋርካ ፍሬ የመጣችበት መንገድ ሳይታወቅ በአንድ ቋጥኝ ላይ ትወድቃለች፡፡ ይህች እናትና አባቷን የማታውቅ ንፋስ ወይም ወፍ ያመጣት የዋርካ ፍሬ ልቧ ትልቅ ነው፡፡ እናትና አባት ባይኖራትም የወደቀችበት አለት ላይ መብቀል ትጀምራለች፡፡ ለመብቀል የሚያስፈልጉ ነገሮች ማለትም አየር ውሃ ሙቀትና አፈር ቋጥኙ ላይ ተሟልተው አይገኙም፡፡ ቋጥኙ ላይ የወዳደቁትን የሌላ ዛፍ ቅጠሎች ንፋስ ያመጣውን አቧራ የሌሊቱን ጤዛ በመጠቀም መብቀል በማይቻልበት ሁኔታ ያቺ ፍሬ መሸፈኛዋን ውስጥ ሥሯ ወደታች ቀንበጧ ወደ ላይ ማደግ ይጀምራል፡፡

በደረቅ በጋ አለቱ እንደምጣድ ሲግል እንኳ ትንሿ ዋርካ ተጠብሳ አመድ አትሆንም፡፡ እነዚያን የትኩሳት ወራት አለቱን የሙጥኝ ብላ ታሳልፋለች፡፡ ይህ ሲሆን ሥሩ ፊታ አይደለም በሥሮቿ እንደብረት ጠንክራና ድፍን የሆነውን አለት እየታቀፈች ለግዙፉ አለት ሳይታወቀው ልብ ሳይላት ትልቅ ሥራ ለነገ ውጤት ትሠራለች፡፡ እሚሰነጠቀውን እየሰነጠቀች እሚታቀፈውን እየታቀፈች በቋጥኝ ላይ የበቀለችው ዋርካ መኖሪያዋን በዚያ ታደርጋለች፡፡





ከቁመቷ ይልቅ ሥሯ ረዝሞ በገደል ላይ ተንጠልጥላ ትኖራለች፡፡ በገደል ላይ ተመቻችታና ገዝፋ ከመታየቷ በፊት በብዙ መከራ ሥሯ እየደማ የማይታለፉ የአመታት መከራ ታልፋለች፡፡

ትንሹ ገርበሌ በእግዚአብሔር ፀጋ በአለቱ በክርስቶስ ላይ ለመብቀል ሥርና ቅርንጫፍ አውጥቶ እንደዛሬው ተንገርጎ ለብዙዎች የእሮይታ ጥላና ማረፊያ ከመሆኑ በፊት ለአመታት ብዙ ፈተናዎችና መከራዎችን አሳልፏል፡፡ በዚሁ ሁኔታ ቤተሰብና የካባቢው ኅብረተሰብ ስለጠላውና አንቅሮ ስለተፋው ከዚያም ሀገር እንዲወጣ ስላስገደዱት ለሁለተኛ ጊዜ ከቤት ወጥቶ መንገድ ጀመረ፡፡ “ወዴት እንደምሄድ ሳላውቅ መፅሐፍ ቅዱሴን ብቻ ይዤ ወጣሁ”፡፡ በማለት ያለ ስንቅ ሳንቲም ወይ መቀየሪያ ልብስ መለመላውን መንገድ የጀመረው ያ ብላቴና፡፡ ከወላጆቹ ቀጥሎ አሉኝ የሚላቸው ክርስቲያን ወገኖችን በመሆኑ ወደነሱ በመሄድ የገጠመውን ስደት ማስረዳትና ምን ማድረግ እንዳለበት በመወያየት ምክር ለመጠየቅ ወ/ዊ ዱሬሳ ዲንሳ ወደሚያገለግልበት ፀሎት ቤት መንገድ ጀመረ፡፡

ከመንገዱ ርዝመትና ስደተኛውም ከነበረበት ሁኔታ ማለትም በልቶ ጠጥቶ ተሸኝቶ ሳይሆን ተገፍትሮ የወጣ በመሆኑ ራበው፡፡ ደከመው፡፡ በጫካ ውስጥ በምታልፈው ቀጭን መንገድ ከድካም በቀር ምን ይገኛል፡፡ የዛፍ ፍሬ ፍለጋ ግራና ቀኝ ሲያማትር ፍሬው የተንዠረገገ የበሰለ የዶቅማ ዛፍ አየ፡፡ ተጠጋው፡፡ ተስፋ አስቆራጭ ነገር፡፡ ዛፉ በጣም ረጅም ሲሆን ረሀብተኛውና የበሰለው ፍሬ በማይገናኙበት ርቀት ላይ ናቸው፡፡

ለልጁ ይህን ዶቅማ በልቶና በርትቶ መጓዝ ግድ ነው፡፡ ስለሆነም ፍሬው እንዲረግፍለት የሚወደውን የኢየሱስን ርዳታ ፈለገ፡፡ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ ይህን ፍሬ የሚያራግፉ ወፎች ላክልኝ" ብሎ ከማለቱ "ከዛፉ ስር ፈቀቅ ብለህ ቁም" የሚል ድምፅ ሰማ ኢየሱስ በሾሉ መንቆራቸው እየወጉ ፍሬ የሚያራግፉ ወፎች ማዘዝ አላስፈለገውም፡፡ ለዚህ ታማኝ ሎሌው ከወፍ የተረፈ ደካማ መልስ ሳይሆን በፊቱ ማዕድ አቀረበለት፡፡ ግዙፉ የዶቅማ ዛፍ በጎርቦሌ ፊት እንዲያጎነብስ ታዘዘ፡፡ ልጁ ወደቆመበት አቅጣጫ የተንዠረገገ ብስል ፍሬ የተሸከመው ዛፍ እንደግማሽ ጨረቃ ጎብጦ ተጎነበሰ፡፡ የጎርቦሌ ሰውነት በድንጋጤ ራደ፡፡ ልቡ ከአቅሟ በላይ ዘለለች፡፡ እግሮቹ በቆሙበት ቦታ ላይ መንቀጥቀጥ ጀመሩ፡፡ በአይኑ ፊት የተፈፀመውን ነገር ማመን አቃተው፡፡

ጌታን ያውቀዋል፡፡ በሥጋ አይኑ እያየው አብረው ውለው ያድሩ የነበረበት ወቅት ነበር፡፡ በቀሪ ዘመኑ ሁሉ ሳይለያው በተዐምር የተሞላ ሕይወት እንደሚኖር የገባው አሁን ነው፡፡ ለረሀቡ በፊቱ ካጎነበሰው ብስል ፍሬ ይልቅ ሀሳቡን የወሰደው የጌታ ቅርብነት በተለይ ዘመድ አዝማድ በገፋውና ባሳደደው በዚህ ጊዜ የማይለይ ወዳጅና ረዳት ኢየሱስ መሆኑ ለወደፊቱም መታመኛው እንደሆነ ተረዳ፡፡ "ጌታ ምን ያህል እንደሚወደኝና ብቻዬን ነኝ ብዬ በምንከራተትበት ምድረበዳ ከኔ ጋር መሆኑ አጠገበኝ ጥቂት ብቻ በላሁ፡፡ ከእንግዲህ ወዲህ ማንም ቢጠላኝ እግዚአብሔር ከኔ ጋር መሆኑ አጠገበኝ፡፡ ጌታ ከኔ ጋር በመሆኑ ዋስትና ያለኝ ሰው እንጂ የባዘነ ተንከራታች አለመሆኔ ከመብሉ ይልቅ አበረታኝ አደሰኝ"





በማለት በዮሐንስ ዘጠኝ ሰላሳ አምስተኛው ቁጥር ላይ የተፈወሰውን አይነስውር አይሁድ ከመሀላቸው ባስወጡት ጊዜ ወደሱ መሄዱን በማስታወስ "ኢየሱስም ወደ ውጭ እንዳወጡት ሰማ..." የሚለውን ያስታውሳል፡፡

ስደተኛው ልጅ ከዶቆማው ፍሬ ከበላም በኋላ አልፎት ሲሄድ ቀና አላለም፡፡ አጎንብሶ ቀረ፡፡ እንደዲጋን ጎብጦ የገርቦሌ ዶቅማ እየተባለ ሲኖር ሲኖር ልጆችና ሴቶች እየፈለጡ ጨረሱት፡፡ እግዚአብሔርን በሚቀረን መንገድ እየኖሩ እንደሆን መስክሮ መስክሮ ጉቶ እስኪሆን ኖረ፡፡ "የገርቦሌ አምላክ" "የገርቦሌ ዶቅማ" ለብዙ ጊዜ በትንሹም በትልቁም የተባሉና የተነገሩ ቃላት ናቸው፡፡

ወ/ሮ ዱሬሳ ዲንሳ ቤት እንደደረሰ ወገኖች በዙሪያው ተሰብስበው አንገቱ ላይ እየተጠመጠሙ ተሳሳሙ ተላቀሱ፡፡ በተለይም ተሰዶ መምጣቱን ሲነግራቸው ለጌታ በመሰደዱ ደስ ሲላቸውም በልጅ አቅሙ በመሆኑ ሳሱለት አዘኑለትም፡፡

በጥቂት ቀን ሁሉን ረስቶ ከወገኖች ጋር ሲያመልክና ሲፅናና ሰነበተ፡፡ ወ/ሮ ዱሬሳ ለአገልግሎት በሚሄርበት ቦታ ሁሉ ይህን ስደተኛ ልጅ የሚያስጠጋ ሰው ካለ በማለት ሲያፈላልግ ቆይቶ አንበሳ አጋ የሚባል ወንድም ሊያስጠጋው ፈቃደኛ በመሆኑ ወደዚያው ተወሰደ፡፡ አገሩ ደጋ ሲሆን በጣም ደን ይበዛዋል፡፡ ለማንኛውም ወንጌላዊው በዚህ ወንድም ቤት ስደተኛው እያገለገለ እንዲኖር አደራ ሰጥቶት ወደ አገሩ ተመለሰ፡፡

በአንበሳ አጋ ቤት የገርቦሌ ሥራ ወደ ማሳ በመሄድ እህል ከአውሬ መጠበቅ ሲሆን ከዋለበት ሲመለስ የማገዶ እንጨት ለቅሞ

ተሸክሞ ይመጣል፡፡ ከወንዝ የመጠጥ ውሃ በትክሻው በመሸከም ይቀዳል፡፡ ማታ ማታ እግር ያጥባል፡፡ ከዚህ ሁሉ በኋላ ራት በልቶ እንደሌሎች ወደ መኝታ አይሄድም፡፡ ያካባቢው አማኞች የሚፀልዩባት ቤት ስላለች ወደዚያች በመሄድ ሲፀልይ ያድራል፡፡ ሲነጋም ትናንት እንዳደረገው ሁሉ የተግባርና የህይወት ዙር ድግግሞሹ ይቀጥላል፡፡ ሰዎች ሲያገኙ ስለ ጌታ አዳኝነት ይመሰክራል፡፡ በጌታ በማመኑ እንደ ተሰደደ ሁሉ እንደሱ በማመን ስለዘላለም ሕይወት መክፈል ያለበትን ዋጋ ሁሉ መክፈል እንዳለባቸው ይመሰክራል፡፡

"የእርሱን ግርማ አይተን እንጂ በብልሀት የተፈጠረውን ተረት ሳንከተል የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስ ኃይልና መምጣት አስታውቀናችሁ ከገናናው ክብር በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው የሚል ያ ድምፅ በመጣለት ጊዜ ከእግዚአብሔር አብ ክብርንና ምስጋናን ተቀብሏልና፡፡ እኛም በቅዱሱ ተራራ ከእርሱ ጋር ሳለን ይህን ድምፅ ከሰማይ ሲወርድ ሰማን፡፡/2ኛ ጴጥሮስ 1፡ 16 -18/

በማለት ገርቦሌም የራሱን ከእግዚአብሔር ጋር የለውን ልምምድ የጨበጠውን ዕውነት ለሌሎች ይመሰክራል፡፡ ክርስትና የመኖር ልምምድ ነውና ገርቦሌም ልምምዱን በመመስከር ሊታመሙ በመፀለይ ሰዎችን በማስታረቅ ሰውንም እግዚአብሔርንም እያገለገለ ለአንድ ዓመት በዚያ ቆየ፡፡ የጌታም ድምጽ "አትፍራ እኔ ከአንተ ጋር ነኝ" እያለ ያበረታታው ነበር፡፡





በዚህ አይነት ስደተኛው ልጅ በአንበሳ አጋ ቤት ለአንድ ዓመት ከቆየ በኋላ 1968 ዓ.ም ማለቂያ ላይ በጌታ ምሪት ወደ ወላጆቹ ቤት ተመለሰ፡፡ ያ ኮሳሳና መጠጊያ የሌለው ልጅ ይህን ለሚያክል ረጅም ጊዜ በህይወት ይኖራል ብለው ስላላሰቡ ሞቷል እርማችንን እናውጣ በማለት ለተስካር ድግስ እየደገሱ የሚጣል በሬ ተዘጋጅቶ ድንገት በመድረሱ እያለቀሱ በመገረም ተቀበሉት፡፡ በተለይም ተስካር ይደገስና እርም እናውጣ በማለት ግንባር ቀደም የነበሩት አጎቱና እናቱ በጣም ተደሰቱ፡፡ የተጀመረው ድግስ ለደስደሱ ሆነ፡፡ "ሞተ የተባለው መጣ" እየተባለ ተበላ ተጠጣ፡፡

ውሎ አድሮ ሁኔታዎች ወደ ነበሩበት ተመለሱ በብርሃንና በጨለማ መሀል ያለው ቅራኔ ተቀሰቀሰ፡፡ አሁንም ቤተሰቡ በዚህ ልጅ ላይ ነገር ነገር ይለው ጀመር፡፡ "ምናለ የተስካሩ ድግስ ዳር ደርሶ እውነትም ተስካር ሆኖ ነገሩ ቢደመደም" ያሉም ነበሩ፡፡ የዚህን ልጅ ሞት ማወጅ በቀላሉ የሚሳካ ነገር አልሆነም፡፡ እሺ አይሙት ግን በቂመናውስ እያለ ከቀድሞ ሁኔታው የተለወጠ ነገር ይኖር ይሆን በማለት መፈተኛ ጥያቄዎች አቀረቡለት፡፡ "ያ ነገርህ ለቀቀህ ወይ የትስ ነበርክ ያስ የሚያነጋግርህ ተወህ ወይስ እንዳለ ነው" የገርቦሌ መልስ ግን አጭርና ጥያቄዎቹን በአንድነት የሚመልስ ነበር፡፡ "አልለቀቀኝም ያው እንደበፊቱ ነኝ" ሁሉም በመገረም አተኩረው ተመለከቱት፡፡ አይናቸው ያስፈራ ስለነበር የሚያደርገውን ያጣው ገርቦሌ ወደ አንድ ጥግ ሄዶ ለፀሎት ተንበረከከ፡፡ በምድጃው ዙሪያ እሳት ይሞቁ የነበሩት ቤተሰቡ ሊረግመን ነው ብለው ስለፈሩ ከቤት ወጡ፡፡ ብቻውን መፀለይ ቀጠለ፡፡

በዚህ ጊዜ ከንግግር ይልቅ ወደ ጸሎት እያዘነበለ በመምጣቱ ይፈሩት ጀመር ከፍርሃታቸውም የተነሳ የሚጠይቀውን ሁሉ ያለ ማቅማማት ያደርጉለት ጀመር:: የገጠር ኑሮ እንደመሆኑ ሳይሰራ የሚኖር የቤተሰብ አባል ስለሌለ ገርቦሌም በዚህ ወቅት ከብቶች በማሰማራት ያገለግል ነበር:: በሳምንት አንድ ቀን ማክሰኞ ካለበት የሦስት ሰዓት የእግር መንገድ ሄዶ የሞጎረ ፀሎት ቤት አዳር ፀሎት ይካፈላል:: በዚህ ዕለት ቀኑንም በሥራው ላይ እያለ በፆም በፀሎት ይውላል:: እንደተዳፈነ እሳት አሁንም የቤተሰቡ ትንቅንቅ ውስጥ ውስጡን ይግማል:: ማክሰኞ ማክሰኞ በፆም ውሎ ከብት አስገብቶ የሦስት ሰዓት የእግር ጉዞ አድክሞት ተስፋ በመቁረጥ ይቀራል በማለት ከብት ካስገባም በኋላ ሌሎች ሥራዎች በማዳበል ያስመሹታል:: ሲመሽ ደግሞ ጨለማው አይን ቢወጉ አይታይም በጫካ ጨለማን አቋርጦ አይሄድም በማለት ሊያዳክሙት ይጥሩ ነበር::

በርግጥ ሁለት ምሽት ችግር ገጥሞታል:: አንድ ምሽት ያንድ ሰዓት መንገድ ከተጓዘ በኋላ ጨለማው በረታበት መንገዱ ጭቃ ነው በዚያ ላይ ይዘንባል:: በዚህ መሀል የተራቡ ጅቦች መሀል ገባ:: አልፎ አልፎ መብረቅ ብልጭ ይላል:: በአንዱ ብልጭታ ጅቦቹ አራት መሆናቸውን አይቷል:: መሀላቸው ገብቷል:: ፈጥኖ አንድ ነገር ማድረግ አለበት:: ለነገሩ ካንድ አማራጭ በቀር በህይወቱ ብዙ አማራጭ ያለው ሰው አይደለም ይህ ልጅ:: "ጌታ ሆይ እነዚህን ጅቦች አባርልኝ" ብሎ በጨለማው ውስጥ በቆመበት የሚሆነውን ይጠብቃል:: ውጤቱ የሚታወቀው የነጎድጓድ ብልጭታ ሲመጣ





ነው:: እውነትም ብልጭ ሲል ከበውት የነበሩት ጅቦች በሙሉ የሉም እናም መንገዱን ቀጠለ በጨለማው የቀጮኗ መንገድ ሸንጥ ሲጠፋው እንደገና ቆም ብሎ የሚያስገመግመውን የሰማይ ብርሃን ይጠብቅና ሲያበራለት አካሄዱን ያስተካክላል:: እንዲህ እንዲህ ተጉዞ ሕይወት ወደ ሞላበት የሞጎር ፀሎት ቤት ደረሰ::

ሌላው አስቸጋሪ ምሽት ዝናብም ጅብም ያልነበረበት የበጋ ምሽት ሲሆን ቤተሰቦቹ ሆን ብለው እንዲመሽበት የሆነ ያልሆነውን ሲያሰሩት ስላስመሹት ጨለማው ከፋ:: የጫካ ውስጥ ጨለማ ደግሞ ድርብ ነው:: ከአቅም በላይ የሆነ ነገር በገጠመው ጊዜ ሁሉ የወዳጁን እርዳታ መጠየቅ የለመደው ልጅ "ጌታ ሆይ በጨለማ ብርሃን ይብራ ብለህልና እባክህ አብራልኝ" አለ:: ወዲያውኑ ከሚያውቃቸው የብርሃን ምንጮች ሁሉ የተለየ ብርሃን የሚወጣው በራሱም ውብና ሕያው ብርሃን ከላይ ወደመሬት ወረደ:: አካባቢው ሁሉ የቀን ያህል ብረሃን ሆነ:: ከብርሃኑም ውስጥ "አይዞህ አትፍራ እኔ ካንተ ጋር ነኝ" የሚል ድምፅ መጣ:: የመጣው ብርሃን ከገርቦሌ ጋር የሚጓዝና ሀልውና ያለው ነው:: የምሽት አራዊት እንደወትሮው ሁሉ ተረጋግተው ተሰማርተው በነበረበት በድንገት በተገለጠው ብርሃን በመደናገጥ ከወዲያ ወዲህ ሲራወጡ እየተመለከተ መንገዱን ቀጠለ::

ለመጀመሪያ ጊዜ የእግዚአብሔር ክብር በላዩ ላይ የወረደውና የዳሰሰው በዚህ ሌሊት ነው:: ወደ ፀሎት ቤቱ ልክ በአየር ላይ እንደሚንሳፈፍ በደስታ እየቀዘፈ እንደደረሰ ያ ብርሃን በመንፈስ ቅዱስ ሞላውና ተለየው:: ያገኘው አዲስ ነገር ከሰዎች ተደባልቆ

ሲያወራ እንዳይወሰድበት በጎች ጉሮሮ ውስጥ ገባ በልሳን እየፀለየ ራሱን መቆጣጠር በማይችልበት ሁኔታ ይንከባለላል ይነሳል ይዘላል፡፡ ይንበረከካል፡፡ በዚህ አይነት አንግቶ ማለዳ ወደሚፀልዩት ወገኖች ብቅ አለ፡፡ ልብሱ በበጎች በጠጥና በሽንታቸው ተጨማልቆ ስለነበር የተሻለው አማራጭ ፈንጠር ብሎ የወጣችውን ፀሀይ በመሞቅ ማድረቅ ስለነበረ በዚህ አረፋፈደ፡፡ ቢሆንም በየመሀሉ አዲሱ ቋንቋውና ኃይሉ መኖራችውን ይፈትሽ ነበር፡፡ በዚያ ሌሊት እሱ ብቻ ሳይሆን ያ ክቡር ብርሃን በፀሎት ቤቷ የነበሩ አማኞችን ጎብኝቶ ስለነበረ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉት ሌሎችም ጭምር ነበሩ፡፡

"አንተ መብራቴን ታበራለህና እግዚአብሔር አምላኬ ጨለማዬን ያበራል" /መዝሙር 18፡26/

አሁንም እንደቀድሞው የገርቦሌ ቤተሰብና የአካባቢው ነዋሪ መልሰው ጠሉት፡፡ በሌለበት ተስካሩን ለማውጣት የደረሱት ለካስ ቢኖር አይወዱትም ማለት ነው? "አንተ ከኛ የተለየህ ነህ መሀላችን መኖር የለብህም ሂድልን" አሉት ባንድ ቃል፡፡ በዚያን አመት ማለትም በ1969 ዓ.ም መሆኑ ነው፡፡ ከነበረበት ከኢቡንቱ ያንድ ቀን መንገድ ርቆ ሞጋ ላይ ኮንፈረንስ ተዘጋጅቶ ነበር፡፡ ያኔ አንድ ቤተክርስቲያን ኮንፈረንስ ስታዘጋጅ የአንድም የሁለትም የሶስትም ቀን የእግር ጉዞ በመጓዝ ስንቅ ሰንቆ ሂዶ የእግዚአብሔርን በረከት መካፈል የተለመደ ነበርና አማኞች ወደ ሞጋ ሲሄዱ ካገኘህ አብረህ ትገባለህ ከኛ ጋር ሂድ ስላሉት አብሮ ተጓዘ፡፡ አብረውት የሄዱትን ወንድሞች ስንቅ እየተካፈለ የኮንፈረንሱን ቀኖች ቆየ፡፡ ወደቀኝም



ወደ ግራም ቢባል ግን ወደ ቤቱ ይዞት የሚገባ ሰው አላገኘምና ተመልሶ "ዓይንህ ለአፈር" ወዳሉት ሰዎች ቤት መጣ፡፡

ወ/ሮ ደረሰ ገለታ ለአገልግሎት አገምሳ የሚባል አገር ሲሄድ ይዞት ሄደና ወንድም አምሳሉ ከፍያለው ለተባለ በመዝሙር ለሚያገለግል በሙያው ገበሬ ለሆነ ሰው "ይኼልጅ የዋህና ትሁት ነው በጌታ በማመኑ ከወላጆቹ ቤት ተገፍቶ ነው የወጣው ከጊዜ በኋላ የሚያድግ የእግዚአብሔር ሰው ይወጣዋል አሁን ለጊዜው ማንኛውንም ነገር ከዚህ ቤተሰብ ጋር ሠርቶ ልጃችሁ ሆኖ ይኑር" በማለት አደራ ሰጥቶት ተመለሰ፡፡

ዘማሪ አምሳሉ ከፍያለ ለገርቦሌ አዲስ አልሆነበትም፡፡ ቀደም ሲል ሞጋ ኮንፈረንስ ላይ ሲዘምር አይቶታል፡፡ እንደውም በመዝሙር አገልግሎቱ በጣም ተማርኮ "ምነው ጌታ የነሱን ቅባት ለኔ በሰጠኝ" በማለት በዝማሬ ለማገልገል ምኞቱን ገልጿል፡፡ በርግጥ በዝማሬ የመጀመሪያዎቹ የአገልግሎቱ አመታት ላይ ያገለግል ነበር፡፡ በዚያን ግዜ በስደት ከኢቡንቱ ይልቅ አገምሳ ይሻል ስለነበር ከእርሱ ወረዳ ተሰደው በመምጣት በሰው ቤት በነፃ እያገለገሉ ጌታን ያመልኩ የነበሩትን የቀደሙትን ደሱ ሶሪና ቶሎሳ ሶሪ የተባሉትን ወንድማማች ስደተኞች እዚያው አገኛቸው፡፡ እርስ በርሳቸውም ይፅናኑ ነበር፡፡

እዚህ ወ/ም አምሳሉ ቤት የገርቦሌ ዋንኛ ተግባር ከብቶች መጠበቅ ሲሆን ከዋለበት ዱር እግረ መንገዱን እንጨት ለቃቅሞ ይገባ ነበር፡፡ ማታ ማታ እግር ማጠብም እንደተጠበቀ ቆይቶ፡፡ የዚህ ወቅት ከባዱ ሥራው ከወንዝ ውሃ ቀድቶ በገንዳ ለከብቶች

ማጠጣት ሲሆን ከመንጋው ብዛትና ከገርበሌ ጡንቻ መሳሳት አንፃር እውነትም አድካሚና ሰዓታት የሚፈጅ ሥራ ነበር፡፡ ይኼ ልጅ ከሲታ ነው እንኳን ወደ ጡንቻው ወደ ሆዱ በቂ ነገር ሳይገባ ነው ያደገው፡፡ የቤተሰብ ፍቅር ያላየ በልቶ ያልጠገበ እየተሳቀቀ እየፈራ እየተንከራተተ የኖረ በአጥንቱ ላይ ከቆዳ በቀር ሥጋ የሌለበት ከስማና በትር እንኳ አጠንክሮ መያዝ የማይችል እንደነበር በዚያን ወቅት ያዩት ይናገራሉ፡፡ ይኼው ልጅ ነው እንግዲህ ጧት ከብት ሲያስወጣ በበላው ውሎ የሚሰራውን ሁሉ ሠርቶ ማታ ከእህል የሚገናኘው፡፡

አገምሳ በቆየባቸው በነዚያ ሦስት አመታት ያሳለፋቸው ቀናት የብቸኝነት የርሃብ፣ ከፀሀይ ቃጠሎና በዝናብ ጊዜ ብርድ በራቁትነትና በባይተዋርነት የኖረባቸው ናቸው፡፡ ይህን ሁሉ ችግር አዳምጦ ወደ ኋላ ቢል ከጌታ መለየት ነው ብሎ ስላመነ ጨክኖ የማይችለውን እያደረገ ሦስት አመት ኖረ፡፡ በነዚህ ሦስት አመታት ያገኘው ደሞዝ ጌታን ማምለክ መቻሉ ነው፡፡ ለዚህም በሳምንት እሁድ ፀሎት ቤት በመሄድ ያመልካል፡፡ ሁልጊዜ ማታ ማታ የአሳዳሪውን እግር ካጠበ በኋላ አቶ አምሳሉ ከእግዚአብሔር ቃል ያነቡለታል የእግዚአብሔርን ቃል መስማት በጣም በጣም ያስደስተዋል፡፡ እንዲያነቡለት ይጠይቃል እሳቸውም ይወዱት ስለነበር በደስታ ያነቡለታል፡፡ እግሮቻቸው መሀል አስቀምጠው እራሱን እየደባበሱ ያነቡለታል፡፡ ከልጆቻቸው ይልቅ ይወዱታል ከውጭ ሲመጡ መጀመሪያ የሚጠይቁት ገርበሌን ነው፡፡ የቤታቸው ሥራ የከበደው ጠልተውት ሳይሆን የገጠር ኑሮ ዘይቤ በመሆኑ ነው፡፡





ሁሉም በየተሰማራበት እንዲሁ ይፋግራል፡፡

"በዚህ ቦታ ስኖር የተማርኩት" ይላል ገርበሌ "ዕምነትና ፅናት በመከራና በርሃብ ፀንቶ መቆምንና ትዕግስት ነው፡፡ ጧት በበላሁት ሙሉ ቀን ውዬ ርቦኝ ስገባ እንጀራ አይቀርብልኝም ነበር፡፡ የቤተሰቡን እግር አጥባለሁ ጥጆችና በጎች አስገባለሁ፡፡ በመጨረሻም የምጓጓለትን የእግዚአብሔርን ቃል ንባብ ከጋሼ እሰማና ራት በልቼ እተኛለሁ፡፡ የጌታም ድምፅ ሁልጊዜ ይመጣልኝ ነበር፡፡ "አይዞህ ይህ ያልፋል እንድትማር ነው እንጂ ረስቼህና ጥዬህ አይደለም" በማለት ያፅናናኝ ነበር እኔም እፅናና ነበር"

በ1960ዎቹ መጀመሪያ በአሙሩ በኪረሙና በአገምሳ ከፍተኛ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ (ሪቫይቫል) ተነስቶ ነበር፡፡ ጠንቋዮችና ቃልቻዎች ሳይቀሩ ሥራቸውን እርግፍ አድርገው በመተው ወደ ጌታ ይሮጡ ነበር፡፡ በየ ገጠሩና በየመንደሩ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የማዳን ክንዱ በግልፅ ይሰራ ነበር፡፡ አጋንንት የነበሩባቸው ሰዎች ገና ወደ መንፈሳዊው የአገልግሎት ቦታ ከመድረሳቸው በፊት በመንገድ እያሉ እየጮኹ ይወጣላቸው ነበር፡፡ በ1962 ዓ.ም በዚያ ሰማያዊ ጉብኝት ተደራሽ ከሆኑት ገበሬዎች አንዱ አምሳሉ ከፍያለው ሲሆኑ ጌታንም የተቀበሉ በዶ/ር ኃይሌ ወ/ሚካኤል አገልግሎት ነው፡፡ ውሎ ሲያድር እኚህ ሰው በጌታ እየበረቱ መጡና በዝማሬ ያገለግሉ ጀመር፡፡ እንግዲህ ስደተኛው ገርበሌ ወደ ቤታቸው በጥገኝነት እንዲኖር ሲመጣ የነበረበትን ሁኔታ እንዲህ በማለት ያስታውሳሉ፡፡

"ሰርቶ መብላት የማይችልበት ዕድሜ ላይ ነበር፡፡ የከሳና የሚንቀጠቀጥ እጆቹ በእከክ የቆሳሰሉ ስለነበሩ በትር እንኳ መያዝ

አይችልም፡፡ እግዚአብሔር እኔን አባት አድርጎ ከሰጠው እሆንለታለሁ በማለት በፍቅር ተቀበልኩት፡፡ እውነትም ከልጆቼ ይልቅ እየወደደድኩት መጣሁ፡፡ ማታ ማታ እግሬን ካጠበ በኋላ "ደክሞሀል?" ይለኛል "አልደከመኝም ስለው መፅሐፍ ቅዱስ አንብብልኝ ይለኛል፡፡ የእምነት ጀግኖችና አባቶች ስለሆኑት ስለነ ዳዊት፣ ሙሴ፣ አብርሃም፣ ዳንኤልና ኤልያስ መስማት በጣም ይወዳል፡፡ ማንም ቢያዘው እሺ ከማለት ውጭ እምቢታን ስለማያውቅ "እሺ መጣ" የሚል ቅፅል ስም ወጥቶለት ነበር፡፡ ነገራ ከሚባል ጓደኛው ጋር እምነትን እንለማመድ እያሉ በእሾህማ ቁጥቋጦ ውስጥ በባዶ እግራቸው ይሮጡ ነበር፡፡ የነገራ እግር ደም በደም ሲሆን የገርባሌ ግን በእሾህ አይወጋም ነበር፡፡ ከሦስት አመት ቆይታ በኋላ ጌታ ተመለስ ስላለው ወደ አገሩ ተመለሰ እኛም በሰቀቀን ሳንጠግበው ተለየነው፡፡" በማለት አቶ አምሳሉ አጫወቱን፡፡

በ1971 መጨረሻ ላይ ሁሌም የሚመራው ያ ድምፅ "አሁን ይበቃሀል ውጣ" አለው፡፡ ቤተሰቡም አካባቢውም እየወደደው ወደ ኢበንቱ ለመመለስ ተነሳ፡፡ 1972 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ ወደ ወላጆቹ ተመለሰ፡፡ ከአካባቢው ወገኖችም ጋር ተደባለቀ፡፡ በብቸኝነት ከእንስሳት ጋር ከመዋል ከወገኖች መዋል ተጀመረ፡፡ በየቦታው መንፈሳዊ ስብሰባዎችን ለመካፈልና ለመዘዋወር እግሩ ተፈታ፡፡ ከቤተክርስቲያን ወደ ቤተክርስቲያንም መሪዎች መልዕክት አሲዘው ይልኩት ጀመር፡፡ ስልክ በሌለበት በዚያን ጊዜ ገርባሌ ፈጣን መልዕክተኛ በመሆን ይላላክ ጀመር፡፡ መንፈሳዊ ስብሰባዎችም ሲኖሩ የተሳታፊዎች እግር በማጠብ ውሃ በመቅዳት ለማዕድ መሰናዶ የሚያስፈልጉ ነገሮችን በማዘጋጀት እግዚአብሔር ለወቅቱ ወዳዘጋጀለት አገልግሎት በመሻገር ብቅ አለ፡፡





# የአገልግሎት ጅማሬ

በወቅቱ ማንም ሰው ያለ ሥራ ወይም ያለ ትምህርት መቀመጥ የለበትም የሚል የመንግስት መመሪያ ወደ ቀበሌዎችና ወደ ገበሬ ማህበራት ወርዶ ስለነበረ የሆሮሙው ገርባሌም ት/ት ቤት ይግባ ተባለና ገባ፡፡ የገሊላ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት በቀጥታ የሁለተኛ ክፍል ተማሪ አድርጎ ተቀበለው፡፡ በወገኖች ቤት ተቀምጦ መማር ጀመረ፡፡ ያኔ ስልክም ፖስታም ለአገሩ ቤተኛ ስላልነበሩ ከቤተክርስቲያን ወደ ቤተክርስቲያን ከመሪዎች ወደ መሪዎች የሚላላከውና መልዕክት የሚያደርሰው ፈጣኑ ተመራጩ መልዕክተኛ እሱ ሆነ፡፡ ሲልኩት ይነቃቃል ደስ ይለዋል፡፡ ቁልቁለቱን ወርዶ ዳገቱን ወጥቶ ጫካውን ሰንጥቆ ከተፍ ይላል፡፡ በዚህ ጊዜ ያካባቢው ፀሎት ቤቶች መሪዎችና አገልጋዮች በዚሁ አጋጣሚ የበለጠ እያወቁት መጡ፡፡ በት/ቤትም በተማሪዎችና በመምህራን የሚወደድ ተማሪ ሆነና አለቅነት ተመረጠ፡፡ የሁለተኛ ክፍል አለቃ ገርባሲ ሂርጳ፡፡ ጴንጤ የማይወደድበት ዘመን ቢሆንም የሁለተኛ ክፍሉን አለቃ ግን ይወዱት ነበር፡፡ የእግዚአብሔር ፍርሃት ከእርሱ ጋር ስለነበር ለሁሉም ቢሆን ይህ ልጅ አይን የሚገባ ሰው ነበር፡፡ በእርሱ ባህሪ ከተማረኩትና ከሚወዱት መምህራን አንዱ የክፍል መምህሩ የነበሩት ጌታቸው ጃሎ ሲሆኑ የእርሱ መንፈሳዊ ሕይወት ተፅዕኖ የኋላ ኋላ በጌታ እንዲሆኑ ረድቷቸዋል፡፡

በት/ቤት በቆየባቸው ሶስት አመታት (1973-1975 ዓ.ም) ከትምህርት ባሻገር መንፈሳዊ አገልግሎትም መስጠትና መለማመድ

የጀመረበት ጊዜ ነበር፡፡ የክፍል አለቃና ተወዳጅ ተማሪ ቢሆንም አገልግሎት ካለበት ለወር ለሁለት ወርና እንዳንዴም ከዚያ ለበለጠ ጊዜ ጠፍቶ ይመለሳል፡፡ ተማሪዎችም መምህራኑም "እንኳን ደህና መጣህ" ከማለት ያለፈ ምንም አይሉትም፡፡ ምክንያቱም ስውየውም ሥራውም የታወቀ ነበርና ፡፡ ያኔ ነበር አካባቢውን ከማገልገል አልፎ ከአድማስ ባሻገር ዘልቆ አባይን ተሻግሮ ጎጃምን ለመድረስ የሄደው፡፡ ድሪባ ዋቅቶላ ከሚባል አገልጋይ ጋ ተንበርክኮ የቤተክርስቲያን መሪዎች ፀልየውላቸው ላኳቸው፡፡ ያኔ መሪዎች አገልጋዮችን ሲልኩ ስንቅ አይሰጡም "መቀየሪያ ልብስና አቁማዳ አትያዙ ተብሏልና እግዚአብሔር ከናንተ ጋር ይሁን" ብለው ይሰዷቸዋል፡፡ የሚያስይዟቸው ነገር ቢኖር ለላብ መጥረጊያ መሀረብ ለምራቅ መሰብሰቢያ ከረሜላ ከአስር ሳንቲም እስከ አንድ ብር የሚደርስ ገንዘብ ባትሪ ከነድንጋዩ ነበርና እነዚህም ሲላኩ የተሰጣቸው ይኼው ነው፡ "ስለሚሰጠን ነገር አስበን እናውቅም እንደውም አገልግሎትና ማግኘት እንዲህ እንዳሁኑ አንድ ላይ አይታሰቡም ነበር፡፡ ዋናው ኩራታችንና የነፍሳችን ምኞች ፀሎታችንም የጌታ መንፈስ መፍሰስ፣ የነፍሳት መዳን የመከራውና የስደቱ ዘመን ማጠር ነበሩ" ይላል ያን ዘመን ሲያስታውስ፡፡

ከገሊላ ተነስተው በኢንጂ አድርገው ቄሎን አቋርጠው አባይ በረሀ ረባዳው የጎሙዞች አገር ደረሱ፡፡ ምግብና መጠለያ ከጉሙዞቹ እየተለገሱ አባይን ከሁለት ቀን ቆይታ በኋላ በታንኳ ተሻገሩ፡፡





ጎጃም መተከል እንደተሻገሩ በቡለንና በድባጤ በወገኖች ቤት እያረፉ አካባቢውን በወንጌል ማገልገል ጀመሩ፡፡ ከህዝቡ ጋርም ለመመሳሰል የሽናሻ አማኞች በአለባበስ አመሳሰሏቸው፡፡ ብዙ ሰዎች የጌታ ኢየሱስን አዳኝነት አምነው ዳኑ፡፡ በርካታ በሽተኞች በሰው ሸክም ወዳሉበት ቦታ ይመጡ ነበር፡፡ አገልጋዮቹም "በጌታ ስም ተፈወሱ" ከማለት ባለፈ የተራዘመና ሥርዓቱን የጠበቀ ፀሎት አያደርጉላቸውም ነበር፡፡ ግን ወዲያውኑ ሕሙማኑ ከማንኛውም በሽታ ይፈወሱ ነበር፡፡ ጌታም ከነዚህ ብላቴኖች ጋር ስለነበር ብዙ ድንቅና ተዐምር ይደረግ ነበር፡፡ በዚህ ዓይነት ለዳኑት መፅናናት ላላመኑት መዳን ለታመሙት ፈውስ በመሆን ለስድስት ወር ከቆዩ በኋላ አገልግሎታቸው ሲያልቅ "ከወለጋ የተሻገሩ ጴንጤዎች ተማሪዎችን አበላሹ" የሚል ወሬ ወደ አውራጃው አኢወማ ቢሮ ደርሶ ኖሮ የአውራጃው የአኢወማ ፀሐፊና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሁሉ ሠራዊት ይዘው ድባጤንና ቡለንን ማሰስ ጀመሩ፡፡ በመጨረሻም ያሉበትን አወቁና ሁለቱ አገልጋዮች ወዳረፉበት መንደር ገሰገሱ፡፡ ገርቢሴና ድሪባ ከአገልግሎት ተመልሰው አገር አማን ብለው ምግብ ቀርበላቸው ይበላሉ፡፡ እስራኤልን የሚጠብቅ አይተኛም አያንቀላፋም እንደተባለው የጌታ ድምፅ በገርቢሴ ጆሮ "ቶሎ ቶሎ ብሉና ውጡ" አለው፡፡ "ቶሎ ቶሎ ብላ ጌታ ከዚህ ሂዱ ብሎናል" አለው የመልዕክቱ ተቀባይ ለጓደኛው ለድሪባ፡፡ ጎረስ ጎረስ አድርገው ያረፉበትን ቤተሰብ ተሰናብተው ያባይን ቁልቁለት የመንከባለል ያህል ተያያዙት፡፡

"እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ባይሆን
እስራኤል እንዲህ ይበል
እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ባይሆን
ሰዎች በእኛ ላይ በተነሱ ጊዜ
ቁጣቸው በላያችን በነደደ ጊዜ
በዚያን ጊዜ ሕያዋን ሳለን በዋጡን ነበር
በዚያን ጊዜ ውሃ ባሰጠመን ነበር
በዚያን ጊዜ የጎርፍ ውሃ በነፍሳችን ላይ ባለፈ ነበር፡፡
ለጥርሳቸው ንክሻ ያላደረገን እግዚአብሔር ይመስገን
ነፍሳችን እንደወፍ ከአዳኝ ወጥመድ አመለጠች
ወጥመድ ተሰበረ እኛም አመለጥን
ረድኤታችን ሰማይና ምድርን በሠራ በእግዚአብሔር ስም ነው" /መዝሙር 124፥1-8/

ብዙም ሳይቆይ አገልጋዮቹ ያረፉበት ቤት ተከበበ፡፡ የሚፈለጉት ባለመገኘታቸው በነሱ እግር አስራ አምስት የአካባቢው ፀሎት ቤቶች መሪዎች ተለቅመው ታሰሩ፡፡

ከስድስት ወር የአገልግሎት ዙረት በኋላ ወደ ገሊላዋ ት/ቤቱ ሲመለስ የአመቱ ማጠቃለያ ፈተና እየደረሰ ነበር፡፡ ወደ ክፍሉም ወደ አለቅነቱም ተመለሰ፡፡ ለአገልግሎት ሲወጣ አለቅነቱን ለአንዱ ለሚያምነው ጓደኛው አሳልፎ ይሰጣል፡፡ ያም ባላደራው ማን ሾመህ ሳይባል የአለቅነት ተግባሩን ይቀጥላል፡፡ የሾመው ዞሮ ሲመለስ በትረስልጣኑን ያስረክበዋል፡፡ ብዙም ሳይማርና ሳያጠና ተፈተነና ወደ 3ኛ ክፍል አለፈ፡፡





በ1974 ዓ.ም ድጋሚ ከድሪባ ጋር ወደ መተከል ድባጤ ተላኩ በጉሙዞች ታንኳ አሻጋሪነት አባይን ተሻግረው ድባጤ ሲደርሱ የታሰሩት መሪዎች ተፈተው ቤተክርስቲያን አድጋና ሰፍታ ቅዱሳኑም በፍቅርና በዕምነት ተሰውጠው አገኟቸው፡፡ አገልግሎታቸውም በጣም የተሳካ ሆነ በዚህ ጊዜ የነበረውን የአገልግሎት ጉዞ ለየት የሚያደርገው የመንፈስ ቅዱስ በሃይል መውረድና የብዙ አማንያን በኃይል መሞላት ነበር፡፡ እዚያው እያሉ የዝናቡ ወቅት ቀድሞ ስለጀመረ አባይ ሞላና መመለሻ አጡ፡፡

ስለዚህ የነበረውን ሌላ አማራጭ በመጠቀም በአዲስ አበባ በኩል ዞሮ መመለስ መሞከር ነበረባቸው፡፡ ወደ አዲስ አበባ መኪና ማግኘት እስከሚችሉበት ቻግኒ ድረስ በእግር መጓዝ ይኖርባቸዋል፡፡ ችግሩ ከመቶ ኪሎ ሜትር በላይ በእግር መጓዙ ሳይሆን አገሩ ቆላማ በመሆኑ በአደገኛ ኮብራ እባብና ጊንጥ የተሞላ መሆኑ ነው፡፡ በእግር እየተጓዙ ከጊንጥ እንዴት ማምለጥ ይቻላል፡፡ እባቡም ቢሆን በአየር ላይ ነው እንደመብረቅ የሚወነጨፈው፡፡ ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ እባብም ጊንጥም ዕድል ፈንታ ስለሌላቸው ሀብቴ ገርቢ በሚባል ወንድም የአቋራጭ መንገድ መሪነት ሁለት ቀን ተጉዘው ቻግኒ ደረሱ፡፡ ባደሩበት ቤርጎ አብዮት ጠባቂዎች ቁጥጥር ሲያደርጉ መታወቂያ ስላልነበራቸው ወደ ጣቢያ ተወስደው ታሰሩ፡፡ ብዙ ጊዜ እምልጠዋቸው ዛሬ እጃቸው በመግባታቸው አይለቁን ይሆን በሚል በጣም ፈሩ፡፡ በማግስቱ ወደ አዛዡ ሲቀርቡ ግን ያልጠበቁት ነገር ሆነ፡፡ ከየት እንደመጡ ለምን እንደመጡ በርጋታ ጠየቃቸው፡፡ ለወንጌል አገልግሎት የሚዘዋወሩ ሰላማዊ ሰዎች መሆናቸውን

ተናገሩ፡፡ ትኩር ብሎ ለደቂቃዎች ከተመለከታቸው በኋላ በርህራሄ ቃል "አሁን እፈታችኋለሁ በደብረማርቆስ አድርጋችሁ በአዲስ አበባ ዞራችሁ አገራችሁ ግቡ ሁለተኛም ወደዚህ አትምጡ" አለ፡፡

ወሀኒ መውረድ የጠበቀት ገርበሊና ድሪባ ለመሳፈሪያ የድባጤ ቤተክርስቲያን ባስያዘቻቸው ብር ተሳፍረው የሞላውን አባይ በጉሙዞች ታንኳ ሳይሆን ጣልያን በሰራው ድልድይ ተሻግረው በሰላሴ በኩል አዲስ አበባ ገቡ፡፡ የአገራቸውን መንገድ ከአዲስ አበባ ተነስተው ቢጀምሩትም የተረፋቸው ገንዘብ ሊያደርሳቸው የቻለው ከአዲስ አበባ መቶ ዘጠና አምስት ኪሎ ሜትር ተጉዘው ጌዶ ላይ ብቻ ነበር፡፡ ገንዘቡ ካለቀ የመኪና መንገድ ለምኔ በማለት ወደ ነቀምት ከሚወስደው መንገድ ወደ ቀኝ በመገንጠል ከጌዶ ወደ ፊንጫህ የሚወስደውን ቁልቁለት በእግር ተያያዙት፡፡ ከፊንጫህ ወደ ላይ ዳገቱን በጃርቴ ጀርደጋ አድርገው ወንጌል እየሰበኩ ለታመሙ እየፀለዩ ከብዙ ቀን በኋላ አሙሩ ደረሱ፡፡ ከአሙሩ ቁልቁል ተዳፋቱን ይዘው ኪረሙ ከዚያም ወገኖችን እየጎበኙና እያፅናኑ በቆቆፌ አልፈው ጊዳ ከጊዳ ኢብንቱ ወደ ጎጃም እተነሱበት በመድረስ ዙርቀለበቱን ገጠሙ፡፡ ከቻግኒ ኢብንቱ ለመድረስ በመኪና ሦስት ቀን በእግር አሥር ቀን የተጓዙ ሲሆን አብዛኛውን የእግር መንገድ አዳር በዛፍ ሥር ነበር፡፡ እግራቸውም ፈንዳድቶ ስለነበር ብዙ ርቀው መሄድ እያቃታቸው በብዙ ችግር ነው የደረሱት፡፡

ገርበሊ ውሃ ቋጥሮ የተላላጠ እግሩን በጨውና በውሃ አንድ ሁለት ቀን ካከመ በኋላ በቀጥታ አለቃ ሆኖ ወደሚማርበት የገሊላ





አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ሦስተኛ ክፍል ተመልሶ ገባ፡፡ በተረፈው ጊዜ ተምሮ ተፈተነና ወደ አራተኛ ክፍል አለፈ፡፡

በ1974 ዓ.ም መጨረሻ አካባቢ አለማየሁ ባይሳ የተባለው መምህራቸው ሚስት በጠና ታመመች፡፡ መምህራቸው የተማረ ሰው በመሆኑ ባለቤቱ እንደ አካባቢው ገበሬዎች ሚስት እስክትሞት ወይ እስክትድን ዝም ብሎ ማየት አልቻለምና ያንድ ቀን መንገድ ያህል ተጉዞ የሚደረስበት ኪረሙ የሚሲዮናውያን ሆስፒታል ሄዳ መታከም አለባት ብሎ በቅሎ ፈልጎ ታማኝ የሆኑ ሀላፊነት የሚጣልባቸው ተማሪዎችን መርጦ ታካሚዋን በበቅሎ አስቀምጦ ላካቸው፡፡ ያስተማሪያቸውን ባለቤት ለማሳከም ከተላኩት ታማኝ ተማሪዎች አንዱ ተማሪ ገርበሊ ነበር፡፡ ተማሪው ሁልጊዜም መንገድ የለመደ ነው፡፡ ሁሌም ለመንገድ ሲነሳ እንደሚያደርገው ለሌሊት ልብስነት የሚያገለግለውን በሸማኔ የተሰራ ፎጣና መጽሐፍ ቅዱሱን ይዞ ት/ቤት ግቢ በጧት ደረሰ፡፡ ፎጣው ጠንካራና ተለቅ ያለ ሲሆን አገልግሎት ሲወጣ የሚለብሰው እንደሌለው ልብ ብሎ ያየው ወንድም አመኑ ነጋሳ ነበር ለሸማኔ ከፍሎ ያሠራለት፡፡ መንገድ ለመጀመር ታማሚዋን በቅሎ ላይ ለማውጣት ግላሱን ሲያስተካክሉ ግላሱ አሮጌና ስስ ስለነበር ለመምህሩ ባለቤት መቀመጫነት ይበቃል ብሎ አላመነበትምና ልዩ ልዩ ጥለት ያለውን የራሱን ፎጣ ከትክክሻው ላይ ፈጠን ብሎ በመውሰድ ኮርቻው ላይ አስተካክሎ አነጠፈው ከዚያ የማስተር ወይም የቲቸር አለማየሁ ባለቤት ተደግፋ ወጣችና ገሚሶቹ ከኋላ ገሚሶቹ ከፊት በቅሎዋን አጅበው ወደ ኪረሙ ክሊኒክ ጉዞ ጀመሩ፡፡

ማታ ኪረሙ ደርሰው በቅሎ ሲያራግፉ የገርቦሌ የሌሊት ልብስ ተንሸራቶ መንገድ ወድቆ ኖሮ ግላሱ ላይ የለም፡፡ ያኔ የጠፋ ነገር ያያችሁ የሚል ማስታወቂያ ት/ቤት ተማሪዎች ባንዲራ ሲያወጡ ወይም ሲያወርዱ ይነገር ነበርና የገርቦሌም የጠፋ ንብረት ተገኘ የሚል ወሬ ከሰማችሁ ለት/ቤቱ አስታውቁ የሚል ማስታወቂያ ተነገረ፡፡ ይህ ፎጣ ከጠፋበት ጊዜ እስከተገኘበት የሆነውን ሁሉ ባገኘው መንገደኛ ተነስቶ የሆነው ሁሉ የታወቀው ኋላ ነው፡፡

አንድ ሰው ያገኘውና አንስቶ ወደ ቤቱ ይወስደዋል፡፡ ሲለብሰው እሳት የለበሰ ይመስል ሰውነቱ ይቃጠላል፡፡ እንግዳና የማይገባው ነገር ሆኖበት ካልለበስኩት ገንዘብ እንኳን ላግኝበት በማለት ለሁለተኛ ሰው አሳልፎ ሸጠው፡፡ የሌሊት መደረቢያ የቀን መጎናፀፊያ አገኘሁ ብሎ የገዛው ሁለተኛው ሰው ልብሱ ባረፈበት ሁሉ እሾህ እንደወጋው ያህል ህመም ይሰማዋል ይሰቃያል፡፡ በዚያ ላይ ሌሊት አንድ ሰው እየመጣበት የባለቤቱን ልብስ መልስ እያለ ያስጨንቀዋል፡፡ ስለዚህ ካልለበስኩት ዋጋዬን እንኳ ልመልስ በማለት ለሦስተኛ ሰው ሸጠው ሦስተኛው ለአራተኛው እንዲህ እንዲህ እያለ ሠላምና ጤና የነሳው ፎጣ ዜና ማስታወቂያ የነገረው መምህር ጆሮ ይደርስና መምህሩ ወደተባለው ቤት ሲሄድ ፎጣው አመሉ እየከፋ ሄዶ የሚነካው ሰው ጠፍቶ አጥር ላይ ተንጠልጥሏል፡፡የመጨረሻዎቹ ሰዎች ካጥሩ ላይ እንዲወስድ ለመምህሩ ነገሩትና አንስቶ ወሰደው፡፡ ለገርቦሌም ተላክለት ሄዶ ንብረቱን ይዞ ገባ፡፡ "ያንተ ፎጣ ከተገኘ እውነትም አንተ የእግዚአብሔር ሰው ነህ እኛም አንዳንደተ እንሆናለን በማለት ለማላገጥ የተወራረዱ ሰዎች ስለነበሩ ተገኘ ሲባል





ለፌዝ የተናገሩት የእውነት ሆኖ ጌታን የግል አዳኛቸው አድርገው ተቀብለዋል፡፡ እግዚአብሔርን ፈሩ ባሪያውንም አከበሩ፡፡ የሚያሳድዱትም ረገብ አሉ፡፡

ገመቹ ፈይሳ፡- የጠፋውን ፎጣ በማጠያየቅና እያደረሰ ያለውን ጉዳት እንደ ዱካ በመከታተል በመጨረሻም እጁ አግብቶ የምስራቹን ለባለቤቱ በመላክ ያበሰረው ስለዚያ ፎጣና አጠቃላይ ሁኔታ የሚከተለውን ብሏል፡፡

"ጌታን ያገኘሁት 1968 ዓ.ም ሲሆን በመምህርነት ኪረሙ በነበርኩበት ጊዜ የማውቀው የገሊላ ት/ቤት መምህር የአለማየሁ ባይሳ ሚስት በጠና ታማ ሚሲዮናውያን ኪረሙ ላይ ወዳቋቋሙት ክሊኒክ በበቅሎ ይዘዋት መጡ፡፡ ካመጧት ተማሪዎች አንዱ ገርቦሌ ነበር፡፡ ይህን ፎጣ አመኑ ነጋሳ የተባለ የተባረከ ወንድም በፀሀይና በብርድ ትንሽ ፎጣ ራሱ ላይ አድርጎ ለሚዞረው ለዚህ አገልጋይ እንዳይበርደው ብሎ በሠላሳ አምስት ብር ያሠራለት ነበር፡፡ በቅሎው ኮርቻ ላይ ከግላስ ጋር ደርበውት መንገድ ላይ ተንሸራቶ ወደቀና ጠፋባቸው፡፡ ስለ ፎጣው መጥፋት ሕመምተኛዋን ባሳረፉበት ቦታ ማታ መፀለይ ጀመሩ፡፡ ያን ጊዜ ሁለት ቀን ያጓጧት በሽተኛ ሶኾች ብዙም አጋንንት ወጣላትና ተፈውሳ አደረች፡፡ በማግስቱ ወደ ሀኪም ከመቅረብ ይልቅ ወደ ቤቷ ተመለሰች፡፡ እኔም የፎጣውን ወሬ የሰማችሁ ጠቁሙኝ በማለት ትምህርት ቤት ባንዲራ ሲሰቀል ሰልፍ ላይ ለተማሪዎች ተናገርኩ፡፡ ከብዙ ክትትል በኋላ ጌታ በእጃችን ላይ ጣለልን፡፡"

ገርቦሌ ገሊሳ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ይማር በነበረበት ወቅት የሚወዱት እንደነበሩ ሁሉ የሚጠሉትና የሚያሳድዱትም ነበሩ፡፡ በትምህርት ቤት ቆይታው አብሮ ያገለግልና መከራውን ይካፈል የነበረው ሰው ሲመሰክር እንዲህ ብሏል፡፡ "የተዋወቅነው 1968 ዓ.ም አካባቢ ነው፡፡ ከብዙ ወንድሞች ጋር ተወልዶ ጌታን በመቀበሉ ሁሉም ጠልተውት በልጅነት ዘመኑ ሁሉ አሳደዱት፡፡ ያደገው በየወገኖች ቤት ነው፡፡ ያኔ ገና ወንጌል ወደኛ አካባቢ ሲመጣ የምናመልከው ዛፍ ሥር ነበር የሚያገለግለንም ሴቀታ ገለታ ይባል ነበር፡፡ ገርቦሌ ያኔ ትንሽ ልጅ ነው፡፡ በዝማሬም ያገለግለን ነበር፡፡ ያኔ ያለሥራ መቀመጥ አይቻልም ስለተባለ የተማሪ መታወቂያ ለመያዝ ሲባል ት/ቤት ገባን፡፡ አገልጋይም እንደሥራፈት ይቆጠር ነበርና፡፡ ሌሊት እያገለገልን ቀን እንማራለን፡፡ የምናመልከው ጫካና ገለልተኛ ቦታ ሄደን ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የምናነበውም ጫካ ሄደን ነው፡፡ ሰው ከመጣብን እየጠናን ነው እንላለን፡፡ አሳዳጆቻችን ጫካ ድረስ ይመጣሉ፡፡ ት/ቤት ይለውጣቸዋል ባለማወቅ ነው እንዲህ የሚሆኑት ተብሎ የደርግ ካድሬዎች "ንቃት" ይሰጡን ነበር፡፡ ሆኖም እየስተማሩንም ለውጥ ባለማየታቸው ተናደዱብን፡፡ ከኛ የሚፈልጉት ለውጥ የእግዚአብሔርን ህልውናና መኖር መካድ ነበር፡፡ በኛም በኩል እግዚአብሔርን እንደማንክድ ስንነግራቸው ከዚያ በኋላ ት/ት ካለወጣቸው ኃይል ይለውጣቸዋል በሚል ከንዳቸውን ያሳዩን ጀመር፡፡ ተይዘን እንድንታሰር መወሰኑንም ሰማን፡፡ ሮብ ዕለት ልንያዝ ቀን ተቆርጦ ሳለ ማክሰኞ ሌሊት ውሳኔውን የሚገለብጥ ክስተት ተፈጠረ፡፡ ሽግሻሽግሌ የተባለ ደም የሚያስቀምጥ በሽታ





ሰፈር ውስጥ ገብቶ ሦስት ሰው ሞቶ አደረ፡፡ ሮብ ዕለት ዋንኛ አጀንዳ የሆነ ነገር ብቅ ብሎ ነገሩ ተለወጠ፡፡ በሽታው እንዳይዛመት የመንግስትና የአብዮቱ ተሿሚዎች ሽርጉድ ለኛ ትንፋሽ ሰጠን ወደ ትምህርትቤትም ያለፍርሃት ሄድን፡፡ በሽታው በተቅማጥ ከዚያም በዝንቦች እንዳይተላለፍ ት/ቤቱ ቀድሞ ሽንት ቤት አልነበረውምና ተማሪዎች ትምህርት አቁመው እንዲቆፍሩ ታዘዘ፡፡

መምህራን ቆመው ስለማያስቆፍሩ ሀላፊነቱን መወጣት ለሚችሉ ተማሪዎች መስጠት አስፈላጊ ሆነ፡፡ ለዚህም የተመረጥነው እኔና ገርቦሌ ነበርንና ወዲያውኑ ወደ ሥራ ገባን፡፡ አካፋና ዶማ ከየቤታቸው የሚያመጡ የሚቆፍሩ በማለት በየሥራ ምድቡ ድልድል አወጣን፡፡ የሽንት ቤቱ ጉድጓድ ተቆፈረ፡፡ ሆኖም በሽታው እዚህ ነው ሲባል እዚያ እየታየ አሳዳጆቻችን ክትትሉን ከኛ ወደ ተቅማጥ አዞሩት እኛን ትተው ሽግሻሽግሌ የወጣበት የገባበት ሪፖርትና ዘገባ አዋከባቸው፡፡ እንድንታሰር በተወሰነበት ቀን ለአለቃነት መሾማችን እነሲድራቅና ሚሳቅ ሚሳኤልንና መርዶክዮስን ውሳኔን የሚገለብጠውንም አምላካቸውን ከኛም ጋር መሆኑን አስታውሶናል፡፡ እምነታችንንም ገንብቷል፡፡"

በ1975 ዓ.ም በቅዱሳን ላይ የተነሳው ስደት እጅግ እየከበደ መጣ፡፡ ይህም ደግሞ የቤተክርስቲያንን አገልግሎትና እንቅስቃሴ ለጊዜውም ቢሆን በአንፃራዊ መልኩ እየገታ ያለበት ጊዜ ነበር፡፡ የሚሰጡ አገልግሎቶች በተቻለ መጠን እንዲቀንሱና የአገልጋዮችም ቁጥር በዚያው መጠን ዝቅ እንዲል ተደረገ፡፡ ጃሌ ላይ የአገልጋዮችና የመሪዎች ስብሰባ ተደርጎ አገልግሎታቸውና

ሕይወታቸው ይገመገም ነበር፡፡ በዚህም ግምገማ የማይፈለጉ አገልጋዮች ይቀነሱ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ቀደም ሲል ከሚቀነሱት አገልጋዮች አንዱ ገርቦሲ እንዲሆን በመሪዎች በሚስጥር ተወስኖ ነበር፡፡ ድካሙ ነው ተብሎ የተጠቀሰው "ይኸ ልጅ በዕድሜም ገና ያልበሰለ በመሆኑና ለዚህ የከበደ የስደት ጊዜ አገልጋይ መሆን አይችልምና ወደቤተሰቡ ገብቶ ይደግ" በማለት ከአገልግሎት ታገደ፡፡

ገርቦሲ ላይ የተወሰነውን አገልግሎት የማቆም ውሳኔ ጉባኤው ሲሰማ አለቀሰ፡፡ ሁለተኛ ወደ አገልግሎት አይመለስም ቤተሰቡም ስለማይቀበለው በሁለት ግፊት የተጣበቀ በመሆኑ እሱም "ከቤት የወጣሁት በስደት ነው አሁንም ብሄድ አይቀበሉኝም፡፡ ቤተሰብ ካልተቀበለኝ ቤተክርስቲያን ካልተቀበለችኝ ወዴት ልሂድ" በማለት አምርሮ ጠየቀ፡፡ የቤተክርስቲያን መሪዎችም "የቤተሰብህን አመል ችለህ ኑር እንጂ እኛ ላንተ ቦታ የለንም" በማለት ቁርጡን ነገሩት፡፡ ይህ ጊዜ ለዚህ ሰው በጣም ልብ የሚሰብር ነው የሆነበት፡፡ ያን ሁሉ መከራ አልፎ አገልግሎት ከጀመረ በኋላ አባይን ከተሻገረ በኋላ እንደገና እጅና እግሩን አጣጥፎ ለመቀመጥ መመለስ፡፡

በፀሎት በሀዘንና በዝምታ የተወሰነ ጊዜ ከቆየ በኋላ 1975 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ወደወላጆቹ ቤት ተመለሰ፡፡ ሁሉም እንደሚያደርጉት በደስታ ተቀበሉት፡፡ ለአንድ ሰሞንም ቢሆን ተንከባከቡት፡፡ ከአባቱ መሬት ቆርሰው ሰጡት "ይህንን እያረስክ ተጠቀም ሚስት ማግባትም ከፈለክ እንድርህለን" አሉት፡፡ "እኔ ያለኝ





አንድ መፅሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው፡፡ ንብረት የለኝ እኔን የምታገባ ሴት አትኖርም፡፡ ባገባ እንኳ የአካል ጉዳተኛ ካልሆነች በስተቀር ሙሉ አካል ያላትና ጤነኛ ሴት እንዴት እኔን ታገባለች ምን ልትበላ ምኔን አይታ" ነበር የገርቦሲ ምላሽ ስለትዳር፡፡ ድሀ ቢሆንም ልብስና ጫማ ባይኖረውም አንድ ጊዜ "ከናንተ ይልቅ ይህ ልጅ የጌታ ፀጋ አለበት እርሱን እወደዋለሁ" ያለችውን ልጅ ለማስታወስ በልቡ የሆነ ነገር ተጫረበት ለነገሩ ልጅቱ ለአገልግሎት ሲሄዱ ያደሩበት ቤተሰብ ሆና ሳለ ስለመንፈሳዊ ፍቅር ተናገረች እንጂ በሥጋ "እወደዋለሁ" አላለችም፡፡

"ጌታ ሆይ የኔ ትዳር ጉዳይ የወንድሞቼ ወይስ ያንተ አጀንዳ ነው" በማለት ጌታን በፀሎት ጠየቀ፡፡ ጌታ ፍቃዱ እንደሆነ አሳወቀው ያለተወዳዳሪም በፊቱ የምትመጣው ያቺ ቀይ ቆንጆ ልጅ አዳነች ብቻ ነበረች፡፡ ደረሰ ገለታ የተባለው አገልጋይ "ጌታን የሚወድ ቤተሰብ ስለሆነ እንበ. አይሉም ምንም ባይኖርህ ከሁሉ በላይ የሆነው ጌታ እንዳለህ ይገባቸዋል ምድራዊውን ሀብት መለኪያ አያደርጉብህም እኔ ራሴ ሰው ጨምሬ ሄጄ እጠይቅልሀለሁ" በማለት በዚያው ሰሞን ሽማግሌዎችን አስተባብሮ ሄደና "እናንተ ጋ ለአገልግሎት የሚመላለሰው ገርቦሲ ልጃችሁን ለትዳር ይጠይቃልና ስጡት" በማለት ጠየቁ፡፡ የአዳነችም ወላጆች ያለአንዳች ማመንታት የገርቦሴን ድህነት ሳይሆን ጌታን አይተውበት ነበርና እሺ አሉት፡፡

ይህ በእንዲህ እያለ በ1976 ዓ.ም ስደቱ ከቀድሞው ይልቅ እየጠነከረ መጣ ክርስቲያን እየታሰሰ ይታሰራል፡፡ መፅሐፍ ቅዱስ

ይቃጠላል፡፡ ያን ጊዜ አገልግሎት በጓዳ ወይም በጫካ በድብቅ ሲሆን መፅሐፍ ቅዱስ በቀፎ ውስጥ ተደበቀ፡፡ "ወንጌል የእግዚአብሔር ቃል ሆይ ቀን መጥቶ እስከምንገናኝ ድረስ ደህና ሁን" በማለት ለአመታት ያልተለየችውን መጽሐፍ ገርቦሌም ዛፍ ላይ ባለው ቀፎ ውስጥ በላስቲክ ጠቅልሎ አኖረ፡፡

ገርቦሌ ቤተሰቦቹ ዘንድ በነበረበት ጊዜ ሁሉ ዋንኛው አሳዳጁና በገባበት ገብቶ የሚያሲዘው የገዛ ወንድሙ ወንድሙ ሂርጳ ነበር፡፡ በሆሮሮ ቀበሌ በተደጋጋሚ አሳስሮታል፡፡ አማኝ ከተገኘ በጥይት ይገደል የሚል ትዕዛዝ የወጣበት ቀበሌ በመሆኑ ገርቦሌም በዚያ ብዙ ጊዜ ታስሯል፡፡ ርሀብ ሲጠናበት ይከዳል በሚል ቀንና ሌሊት ግንድ ላይ ታስሮ እስከ ሦስት ቀን በማቆየት የሚያሳዩት መከራ አንድም ክርስቲያን ወደ ኋላ ማድረግ አልቻለም፡፡ በዚያ ቀበሌ ሰባት ቀንና ሌሊት በፆም በፀሎት ቆይቶ ወደ ወገኖች ሲሄድ በመንገድ ላይ የፓርቲ አባሎች አግኝተው አሰሩት፡፡ ያ እሱ በተደጋጋሚ የታሰረበት የቀበሌ እስር ቤት ኋላ በጣም ትልቅ ቤተክርስቲያን ተተክሎበታል፡፡ በዚህን ወቅት ጴንጤዎችን አድኖ ለቀበሌ የሚያስረክብ ጠመንጃ ይሸለማል ስለተባለ ወንድሙ ሂርጳ ገርቦሌን እየነዳ ለመውሰድ ጊዜ አልፈጀበትም፡፡ አገልጋዩን አሳስሮ ጠመንጃውን አንግቦ በደስታ እየፈነጠዘ ተመለሰ፡፡ እንደገናም ሌላ ጊዜ ይህ ትንሽ ልጅ አገሩን በጠበጠ በላዩ ላይ ቤቱን በእሳት እናቃጥላለን በማለት ሰባት ሚሊሻዎች ሊለኩሱ መጡ እሱም ከቤት ወጥቶ ሄደ፡፡ " ከዚህ ጥፉ ሁለተኛ እንዳትመለስ" አሉት "ወዴት እጠፋለሁ ገና ይህ አገር እግዚአብሔርን በማወቅ ይሞላል"





አላቸው፡፡ ሚሊሻዎቹም በንቀት አዋረዱት ሰደቡት "እግዚአብሔር ከናንተ ጋር ይሁን" ብሏቸው ሄደ፡፡ እነዚያ ሚሊሻዎች ግን ሰው ከማሳደድ ያለፈ በእግዚአብሔር ላይ የተደረገ ተግዳሮት ስለሰሩ በተከታታይ ተጎዱ፡፡ አንደኛው ሰባት ቦታ እባጭ ወጣበት፡፡ ያንደኛው ከብቶቹ ታወሩ፤ ያንደኛው ልጅ ሞተ፤ አንደኛው ብን ብሎ ቤቱን ትቶ ካገር ጠፋ፤ ሊቀመንበሩ ከሌሎች ሁለት ጋር በጌታ አምነው ክርስቲያን ሆኑ፡፡

በገርቦሌ ላይ ከደረሰው መከራ የከፋው በጦር ራስቅሉን የተወጋው ነው፡፡ የጦሩ ጫፍ ከኋላ ራሱ ላይ ተቸክሏል፡፡ ያኔ እንደተወጋ ራሱን ስቶ ወደቀ ሞቷል ተብሎ ተተወ ደሙ በምድር ላይ ተንዠቀዠቀ ወደርሱ የሚጠጋ አልነበረምና ውሻ ደሙን ላሰው፡፡ ከሶስት ቀን በኋላ ተነስቶ ወገኖች ወዳሉበት ቦታ ሄደ፡፡ የራሱ ላይ ቁስል ቀስበቀስ ቢድንም የተወጋበት ቦታ ላይ ከብ ጠጣር ነገር ሆኖ የቀረው ያንን ሁኔታ ለማስታወስ ዛሬም አለ፡፡

ያኔ ያሳደደው ሕዝብ ሁሉ ዛሬ በጌታ ሆኗል፡፡ ኮንፈረንስ አድርገው ጠርተውት ነበርና እዚህ ደሙ የፈሰሰበት ቦታ በሺህ የሚቆጠሩ አማኞች ያሉበት ቤተክርስቲያን ተተክሏል፡፡ ገርቦሌ ይቅር እንዲላቸው ወደዚያ ወስደውት ቀድሞ ያሳደዱትና አይንህ ላፈር ይሉት የነበሩትን ሁሉ ይቅር ብሏል፡፡ ባርኳል፡፡ አሳዳጆቹ ግማሾቹ በሽተኞች ከብቶቻቸው የሚጨነግፉ ደም የሚሸኑ ሆነውባቸው ስለነበር ይቅር ሲላቸው በረከታቸው ተመለሰ፡፡ በዚያ አካባቢ ያሉ ሕዝቦች "እባካችሁ ሲመጣ ለኛም ላኩብን ይቅር

ይበለን" በማለት በመላላክ እንዳላጣፉት በመላላክ እግሩ ላይ ይወድቁ ጀመር፡፡ አሳስሮት ጠመንጃ የተሸለመው ወንድሙ ሂርጳ የተሸለመውን የደርግ ጠመንጃ አቅፎ ቢተኛም በሽተኛ ሆነ ንብረቱ ወደመ ቤቱ በመከራ ተመታ፡፡ ኋላ መካሪ ግብቶት" ያ ሰው ብናሳድደውም አላጠፋነውም የተሳሳትነው እኛ ነን አንድ ሰው እንዴት አገር ተነስቶበት አይጠፋም" በማለት ንስሀ ገብቶ የገርቢሴን አምላክ አከብሯል፡፡ ገርቢሲ ድሮ በቤት የተዋቸውን ጨርቃ ጨርቅ ልብሶች ለበረከት ይሆናሉ በማለት በበረቱ ላይ በማሳው ውስጥ ሰቅሎ ጤናው ተመለሰ ከብቱ ከቀድሞው ይልቅ ተባረከ እህሉ በብዙ እጥፍ ተመረተ፡፡ "ከእግዚአብሄር ጋር ተጣልቼ ነበር ከእግዚአብሔር ጋር ታረቅሁ" ይላል ሰው ስለልዩነቱ ሲጠይቀው፡፡

"በመከራ መካከል እንኳ ብሄድ አንተ ሕያው ታደርገኛለህ" (መዝሙር 138፥7)

ገርቢሲ ከልጅነት እስከ እውቀት ከብዙ መከራና ሞት እግዚአብሔር ጠብቆ እንዳሳለፈው ደጋግሞ ይናገራል፡፡ በወጣትነት ዘመን እየተዘዋወረ ላገኛቸው ወንጌልን በሚሰብክበት ጊዜ እየተጓዘ እየተጓዘ ከአካባቢው ርቆ አባይ በረሀ ወደሚባለው ቆላማ አገር ደረሰ፡፡ ሌሎች ሕዝቦች መሀል፡፡ የዚህ አካባቢ ሰዎች እሱ ከኖረበት የተለየ ባህል አላቸው፡፡ ወጣቶቹ ለማግባት ሴቶችን ሲጠይቁ ወንዱ በርግጥ ለማግባት የተዘጋጀ ወንድ መሆኑን የሚያሳይበት ተግባራዊ ማስረጃ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡ አራት አምስት ወንዶችን ከሌላ አካባቢ በመግደል ከግንባር ጀምሮ ፊትን ጨምሮ እስከታች የእግሮቹ





መለያያ ድረስ ያለውን ቆዳ በመግፈፍ በግቢው ውስጥ ደርድሮ መስቀል አለበት፡፡ ለጋብቻ የተጠየቀችው ወጣት ተገፈው የተደረደሩትን ሰለባዎች ማየት አለባት፡፡ ታይናም "እውነትም ይኼ ወንድ ነው አገባዋለሁ" ትላለች ገድሎ ካልሰቀለ "መቼ ወንድ ሆንክና ነው ጋብቻ የምትጠይቀኝ መጀመሪያ ወንድና ሴትነትህን ፈትሽ" ብላ አሳፍራ ትመልሰዋለች፡፡ ይኼ ደግሞ ለዚያ ሰው ሞት ነው፡፡ የሷ እምቢ ማለት ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ጋርም ለሚኖረው የጋብቻ ጥያቄ "እገሌ ሴት ነህ ብላ የመለሰችህ አይደለህም እንዴ" እየተባለ ገቢያው ይዘጋበታል፡፡ ስለዚህ ወደ ጋብቻ ጥያቄ ሄዶ ውድቅ ሆኖ ከመመለሱ በፊት በቂ ግዳይ በመጣል መደርደር ይጠበቅበታል፡፡

ወንጌል ቦታ አይመርጥም ለአለም ሁሉ የተላከ መልዕክት ስለሆነ ጌታም በከተማ በገጠር በመንደር በገበያ ቦታ ሁሉ እየዞረ ይሰብክ እንደነበር ይህም ባሪያው እንዲሁ እያደረገ አባይ አፋፍ ደረሰና ወደ አንዲት ቤት ጎራ ብሎ ሰላምታ ሰጠ፡፡ ከውስጥ አንዲት አሮጊት ወጣች፡፡ ከላይ እስከታች አየችውና "ና ግባ ልጄ ሚስት ለማግባት ፈልጎ ለእሮጮኛው የሚያሳይትን ግዳይ ፍለጋ ወጥቷል ገና የሚያስፈልገውን ያህል ሰው አልገደለም እንተንም ካገኘህ ይገድልሀል፡፡ እኔ አንተ እንድትሞት አልፈለኩም ሌላ ሰው ገድሎ ያሟላ፡፡ አሁንም እዚህ እያለህ ከመጣ ይገድልሃል ሂድ ወደ ወንዝ ውረድና ጥጥ ልቀምልኝ" በማለት የጥጥ ማሳዋን በሩቅ አመለከተችው፡፡

ጥጡ ወንዙ ዳር ነው፡፡ የፀሐዩ ንዳድ አይጠየቅም እሳት

ነው፡፡ የሚቆምበት መሬት እንደምባድ ግኗል፡፡ አፈሩ አሸዋማ ደለል ሲሆን እዚህም እዚያም ጊንጡ አሸዋውን እየገለበጠ ይወጣል፡፡ ያም ባዶ እግር ማሳረፊያ ቦታ አጣ፡፡ ለባዶ እግሩ ይሰማዋል አንድ ነገር ላይ እንደቆመ ግን አይነድፋትም እዛም ቢቆም ያው ነው እዛም ቢረግጥ ያው ነው፡፡ በዚያ ላይ የጥጡ አገዳ ደቃቅ እሾህ ስላለው እጆቹ ላይ ተከሰከሰበት፡፡ ጠራራ ፀሐይ ስለነበር እሾሁ እንደጦር ቆሞ ይዋጋል፡፡

በዚያ ላይ ሰማይ መስሎ ከበታቹ የተንጣለለው አባይ ሰላም አይደለም፡፡ ጉማሬው ይጨፍራል፡፡ ውሀውን እንደመብረቅ ይሰነጥቀዋል ይጮሃል አባይን እየታገለ አረፋ ባረፋ ያደርገዋል፡፡ ጥጥ ለቃሚው ካለበት ብዙም ያልራቀው የጉማሬ ሰራዊት አካባቢውን ያናውጠዋል ለቃሚውን ጨምሮ፡፡ ከጉማሬ ላይ የተነሱ አይኖች ሌላ ሰራዊት ማየት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የአዞ መንጋ፡፡ በውሃው ዳር ፀሀይ የሚሞቁ አዞዎች ይታያሉ፡፡ አፋቸውን ከፍተው በጥርስና በጥርሳቸው መሀል የተሰነቀረውን ሥጋ ለሚነቅሱ ወፎች ሲመግቡ ማየት ይቻላል፡፡ ግዙፉ አባይ በውስጡ የያዘው ሁሉም ነገር ግዙፍ ነው፡፡ ጉማሬው፣ አዞው ጊንጡ፣ ኮብራውም ቢሆን በአየር ላይ እንደ ላውንቸር ነው የሚወነጨፈው፡፡ አባይ በኃያላን የተሞላ ነው፡፡ ከፀሐዩ ንዳድ ጀምሮ፡፡ በዚህ በረሀ መሞት አያስደንቅም፡፡ የሚያስደንቀው ፈጥኖ አለመሞት ነው፡፡ የአከባቢው ነዋሪዎች አባይን ያመልኩታል የሞት መሳሪያዎቹን እንዲያስታግስ መስዋዕት ያቀርቡለታል፡፡ ገርቦሌ ለአሮጊቷ ወንጌልን ሲመሰክርላትም ያለችው ይኼንኑ ነው፡፡ "የኛ አምላክ አባይ ነው" አባይ ከአቢሲኒያ እስከ





ግብፅ ይመለካል፡፡ አዞና ጉማሬ አባብና ጊንጡ የሱ ኃያላን መላዕክት ሆነው እብረው ይሰገድላቸዋል፡፡ መስዋዕት ይወረወርላቸዋል፡፡

ጥቂት እንደለቀመ አሮጊቷ መጣች "እስቲ የለቀምከው ይበቃሀል ልጄ ና አሁን የልጁ መመለሻ ስለደረሰ ቶሎ ከዚህ አካባቢ ሂድ ሳይገልህ" በማለት እነሱ ከሚበሉት ምግብ ጥቂት ሰጥታ ሸኘችው፡፡ ያሳየችውን መንገድ ይዞ ገሰገሰ የሰማውንና ያየውን ፍልሚያ እያሰበ፡፡ ጊዜው እየመሸ ጨላለመ ወዲያና ወዲህ ቢያይ ማደሪያ የሚሆን ነገር አላገኘም ወደሰዎች ቤት መጠጋትም አልፈለገም ምን ይታመናል፡፡ ድንገት አደናቸው ውስጥ ቢገባስ? ስለዚህ ከሰው ይልቅ አውሬ ባለበት በጫካ ማደር መረጠና ላዩ እንደ አልጋ የተዘረጋ ጠፍጣፋ ዛፍ ላይ ወጣ፡፡ ምሽቱ እየገፋ ሲሄድ የሌሊት ተረኞች ምድሩን ተቆጣጠሩት አንበሳው ያገሳል፡፡ ነብሩ ያስገመግማል፡፡ ከወዲያ ወዲህ በሩቅና በቅርብ ሩጫና ትርምስ ካለበት ዛፍ በታች ያለው አገር የአራዊት መርካቶ ሆነ፡፡ በአይኑ እንቅልፍ አለመዞር ብቻ ሳይሆን እንቅልፍ የሚባል ነገር መኖሩ እንኳ ትዝ ሳይለው ነጋ፡፡ "እስራኤልን የሚጠብቅ አይተኛም አያንቀላፋም" እንደተባለ በእግዚአብሔር ጥበቃ በሰላም ወደ አገሩ ተመለሰ፡፡

"በልዑል መጠጊያ የሚኖር
ሁሉን በሚችል አምላክ ጥላ ውስጥ ያድራል
እርሱ ከአዳኝ ወጥመድ
ከሚያስደነግጥም ነገር ያድንሃልና

ከሌሊት ግርማ
በቀን ከሚበርር ፍላፃ
በጨለማ ከሚሄድ ክፉ ነገር
ከአደጋና ከቀትር ጋኔን አትፈራም" (መዝሙር 91፡1-6)





# አዳነች

አቦ ቶሌራ እሬሶና አዴ ብዙነሽ ደሳለኝ በሆሮ ጉድሩ አውራጃ በሊሙ ወረዳ በስፔራ ሜጢ ቀበሌ ከለቡ ወንዝ ባሻገር ደረቱን ወደ ፀሐይ መውጫ ገልብጦ ባለው መሬት ላይ እተንጣለለው ግቢ ውስጥ ወልደው ከብደው ይኖራሉ፡፡ በአጠቃላይ ሦስት ሴቶችና ሰባት ወንዶች በአጠቃላይ አሥር ልጆች ተወልደዋል፡፡ መተዳደሪያቸው ግብርና ሲሆን በዋናነት ጤፍ በቆሎ ስንዴና ገብስ ያመርታሉ፡፡ በዚያም ላይ የመንጋው ቁጥር ቀላል አይደለም፡፡

ከጎራቸውም አልፎ ወንዙን ተከትሎ አለን አለን የሚሉት ትልልቅ ዛፎች ላይ ተሰቅለው የሚታዩት ቀፎዎች ለቤቱ መታወቂያ የሆነውን ስም "የማርቤት" አሰጥተውታል፡፡ እንግዳ ማር ሳይበላ አይሄድም ነበርና ቤቱ ማርቤት ተባለ፡፡ ከአሥሩ ልጆች አዳነች ሦስተኛ ናት፡፡ "አዳነች" የተባለችበትም ምክንያት የራሱ ታሪክ አለው፡፡ አባቷ ገና ወጣት ሳሉ ክፉ ሰዎች በምግብ መርዝ አበሏቸውና በሽታ ተጠናወታቸው፡፡ ሆዳቸውን ያቃጥላቸዋል፡፡ ሌሊት ያስፈራራቸዋል፡፡ ለብዙ ዓመታት ጤና ያጡ ሰው ሆነው ሲኖሩ የባለቤታቸው አባት አማቻቸው አቦ ደሳለኝ ዱጉማ የመድሃኒት ወሬ ነገሯቸው፡፡ "አሙሩ እሚባል አገር ከሰማይ መድሃኒት ወርዷል ሲባል ሰምቻለሁ እባክህ እስቲ ሂድና ሞክር ልጄ" እንዳሏቸው አቦ ቶሌራም መድሃኒት ተገኝቶ ምን ማመንታት ያስፈልጋል በማለት ስንቅ ተሰንቀና ገና ስም ያልወጣላትን እራስ ሕፃን እናት ይዘው ጉዞ ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ ሆነ፡፡ የሁለት ቀን

መንገድ ተጉዘው አሙሩ ደረሱ፡፡ ሌሎችም እንደነሱ እግዚአብሔር አሙሩ ላይ ወርዷል ተብለው ከሩቅና ከቅርብ በብዛት ይጎርፉ ነበርና ከመንገደኛው ጋር ተደባልቀው እግዚአብሔር ወረደበት ወደተባለው አገር ደረሱ፡፡ በዚያ ኃይሌ ወ/ሚካኤል መኩሪያ/ ሙሉጌታና ሌሎች አገልጋዮችም ጭምር ወንጌልን እየሰበኩ ለበሽተኞች ይፀልዩ ነበር፡፡ ጌታም ታላላቅ ተዐምራትን ያደርግ ነበር፡፡ አጋንንት የነበሩባቸው ሰዎች ገና ወደ አሙሩ የአገልግሎት ቦታ ሲነሱ ጮኸ ይወጣላቸው ነበር፡፡ ደፍሮ እስከ አገልግሎቱ ቦታ ድረስ ተከፍሶ በሰዎቹ ውስጥ አይቆይም ነበር፡፡

ማንም ለማንም ኢየሱስ ክርስቶስ ያድናል ብሎ ሳይመሰክር ያገሩ ሕዝብ እርስ በርሱ እየተጠራራ "አሙሩ ላይ እግዚአብሔር ወርዷል" በማለት ይጎርፋል፡፡ ጠንቋዮችና ቃልቾች ዝንት ዓለም ከገዙት ሕዝብ ትከሻ ላይ እየወረዱ የጥንቆላ ቁሳቁሶቻቸውን እየሰባበሩና እያቃጠሉ ወደ ጌታ ጉያ ይሮጡ ነበር፡፡ ጌታን የግል አዳኛቸው አድርገው በመቀበል በመንፈስ ቅዱስ እየተሞሉ ላልሰማ ለማሰማት ወደ መጡበት ይመለሱ ነበር፡፡

ይህ ቤተሰብ ወደዚህ የሞቀ መንፈሳዊ በረከት ተጎዞ ደረሰ፡፡ ወንድም መኩሪያ ሙሉጌታ በአቦ ቶሌራ ላይ እጃቸውን ጭነው ፀለዩላቸው ጌታም ፈወሳቸው፡፡ ባልና ሚስት አብረዋቸው የሄዱት የአዳነች አክስት አዴ ደበሌ ጌታን ተቀብለው በሽታውን አሙሩ ላይ ጥለው ወደቤታቸው ተመለሱ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የህፃኗ ስም አዳነች ተባለ አባቷ በዚ ጊዜ ድነዋልና፡፡ ወደቤታቸው ተመልሰው በበሽተኝነት ዓመታት የተከማቸውን በርካታ የጣዖት አምልኮ





ማፍረስና ማስወገድ ነበረባቸው፡፡ እንዲሁም አደረጉ ቤቱም የክርስቲያን ቤትና ለአካባቢው የቤተክርስቲያን ጅማሬ ሆነ፡፡ እሳት ከቆሰቆሱት ይነዳልና ያም አካባቢ እየዳነ እሳቸውም የዳኑትን እያገለገሉ ሕዝብ እየበዛ መጣ፡፡"

አዳነች ትንሽ ልጅ እያለች ትዝ የሚላትን እንዲህ ታጫውተናለች፡- "ትንሽ ልጅ ሆኜ አስታውሳለሁ ሰዎች በሽተኞቻቸውን ይዘው ወደቤታችን ይመጡ ነበር፡፡ አባታችንም ይፀልዩላቸውና ተፈውሰው ይሄዳሉ፡፡ ብዙ ጊዜ አጋንንት ጮኸ የሚወጣው በሽተኛው እኛ ቤት ሳይገባ በደጅ ነበር፡፡
አጋንንት የሚያስጮኸው ሰው ስናይ እኛ ልጆች ስለነበርን እንፈራ ነበር ወደ ቤት ገብተን አልጋ ላይ እንወጣና እንሸፋፈናለን፡፡ ያን ጊዜ አገልጋዮች አልነበሩም በፀሎትና በመገሰፅ የሚጮኹት አጋንንት ነበረ "መጡብኝ ተቃጠልኩ" ብሎ የሚጮኸው፡፡ አገልጋዮቹ የቆሙበት ቦታ በክፉ የተያዘ ሰው መቆም አይችልም ነበር፡፡ እግራቸው ያረፈበት መንገድ የተቀመጡበትና ያረፉበት ቦታ ሁሉ "እሳት አለው" ይላል ክፉው፡፡ ሌላ ቀርቶ በአጋንንት የተያዙ ሰዎች የሚፀለይበት ቤት እወስድሀለሁ ሲባሉ እንኳ መንፈሱ ጮኸ ይወጣ ነበር፡፡ ወደ ቤት የሚገቡት ለማምለክ እንጂ በሽታቸው ከደጅ ይቀር ነበር፡፡

ከክፉ መናፍስት እስራት ፈውስ ሌላ ምጥ የጠናባቸው ለሁለትና ለሦስት ቀን ያማጡ ሴቶች ቤት አባታችን ይጠሩና ይሄድ ነበር፡፡ ገና ቤታቸው ሲገባ ይገላገላሉ፡፡ ያን ጊዜ መታገል አልነበረም፡፡ ባንድ ቃል ወይም በመገኘት ብቻ ጌታ ድንቅ ያደርግ

ነበር፡፡ አባቴ ለእርሻ በወጣበት ቦታ እንኳ በቀን ሦስት ጊዜ ተንበርክኮ ይፀልይ እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡ ያኔ ወገኖች በጣም ይፈላለጋሉ ይዋደዳሉ፡፡ ቤታችን ለታመሙ መፈወሻ ለእንግዶች ማረፊያ ነበር፡፡ የአካባቢው ምዕመናን አምልኮና አገልግሎትም ይካሄድ ነበር፡፡ ስለሆነም ከሌላ ቦታ ለማገልገል የሚመጡ አገልጋዮችም ማረፊያና መስተናገጃም መሆን ይጠበቅብን ነበር፡፡ አገልጋዮች ባያገለግሉም እንኳ ለማረፍ ብለውም ይመጣሉ፡፡ በ1972 ዓ.ም ሊያገለግሉ ከመጡት ውስጥ ትንሹ ልጅ ገርቦሌም ነበር፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ለማገልገልም ሲያልፍ ሲያገድም መጥቶ ያርፋል፡፡

ሰደተኛ መሆኑን የሚያውቁ ወላጆቼ በጣም ያዝኑለታል ይወዱታል ቤተኛም ከመሆን አልፎ እንደ ልጃቸው ያዩታል፡፡ ያሳዝን ነበር፡፡

ይህ በእንዲህ እያለ አንድ ቀን ሦስት ወንድሞች ወደ ቤታችን መጡ፡፡ ከእናቴና ከአባቴ ጋር መክረው ሄዱ ጭምጭምታ እንደሰማሁት ነገሩ እኔን ይመለከታል፡፡ ብዙ ቀን ቆይቶ በአሥራ አራት አመቴ ሰዎች ወደተሰበሰቡበት ዋናው ቤት ተጠራሁ፡፡ ያኔ እንጀራ እየጋገርኩ ነበር፡፡ ወንድሜ ገመቹ መጣና "ነይ" አለኝ "እንጀራ እየጋገርኩ ነው ለምንድነው የምመጣው" "ነይ ተይውና ልንሸጥሽ ነው" አለኝ፡፡ ከነሊጡ እያስቸኮለ ወሰደኝ፡፡ አባቴ አንድ ወረቀት ላይ ፈረመ፡፡ ሌሎቹም ፈረሙ፡፡ ገርቦሌም ፈረመ፡፡ ለኔም ቦታ አሳዩኝና ፈረምኩ፡፡ ንግግር የለምና ስለምን በዝምታ የተቀጠ መፈራረም እንደሆነ አልገባኝምና ወደ ምጣዴ ተመልሼ ቆሰቆስኩና





እሳቱን እንደገና አንድጄ ምጣዱ ስትሰማ ነገሩ ሆዴን እየበላኝ አንዴ አሰስኩና በሀሳብ ተውጬ ቀስ ብዬ ወፍራም እንጀራ ከበፊቱ ለየት ያለ ወፍም እንጀራ አሰፋሁ፡፡

ለልብስና ለአንዳንድ ነገሮች የሚያስፈልገውን ገንዘብ ለማግኘት አሰበና አንድ ወንድሙን "ገንዘብ የሚገኘው እንዴት ነው" ብሎ ጠየቀው ገርቦሌ የነገው ሙሽራ "ብትነግድ በአጭር ጊዜ ገንዘብ ልታገኝ ትችላለህ" ብሎ መለሰለት ያም ወንድም "ምን ልነግድ በምንስ ልነግድ ቢለው መያያዣ ገንዘብ ሰጠውና አህያ ከአሙሩ እያመጣህ እዚህ ብትሸጥ ያተርፍሃል አለው፡፡ እነሱ ካሉበት አሙሩ የአህያ ገበያ ሲሄዱ ሦስት ቀን ሲመለሱ ሦስት ቀን ደርሶ መልስ የስድስት ቀን የእግር ጉዞ ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ እናቴ ሲሰሙ" ተው ልጄ አሁን አንተ ምኑን አውቀህ ትነግዳለህ የሰርግ ልብሱንና ጫማውን እኔ እገዛልሀለሁ" ቢሉትም "ተይ እማዬ ቁጭ ከምል ልነግድ" በማለት ቆርጦ ሲነሳ ስንቅ ቋጠሩለትና ገሥግሶ አሙሩ ደረሰ፡፡ ወደል አህያ በሃያ ብር ገዝቶ እየነዳ በሳምንቱ ተመለሰ፡፡ በሪማ ቅዳሜ ገበያ አመጣውና አህያ ተራ ወስዶ አቆመው፡፡ በዚህ ወከባ በዚያ ወከባ ጩኸትና ጫጫታ "ያዝ" እንኪ" መጨባበጥ እጅ መሳሳም መሻሻጥና መግዛት ዙሪያውን ሲመለከት የእሱን አህያ ማንጠይቆ ወይ ፍንከች፡፡ ቀስ በቀስ ገበያው እየሳሳ ሄዶ ይባስ ብሎ ከእርሱ ጋር አንድ ሽማግሌ ብቻ አህያ ተራ ላይ ቀሩ፡፡

"የእኔ አህያ ለምን ገዢ አጣ ሰውም ከጧት እስካሁን አልጠየቀኝም ምን እንከን አዩበት" በማለት ጠየቃቸው፡፡" የንተ

አሀያ የሚሸጥ ኖሯል እንዴ የሚሸጥ ከሆነኮ አንገቱ ላይ ምልክት ማሰር ነበረብህ ለሽያጭ የመጣና ተጭኖ መጥቶ ወደ ቤቱ የሚመለስ አሀያ ወደ ገበያ የወጡበት ምክንያት የሚታወቀው በምልክት ነው" ሲሉት አንገቱ ላይ ሀረግ ነገር ለማሰር ፍለጋ ወደ ቁልቁለት ወረደ፡፡ ይዞ ሲመጣ አሀያው ባዶ ገበያ ላይ ተኝቷል፡፡ ቢያመላክተውም በተበተነ ገበያ ምን ዋጋ አለው ወደ ቤት አሀያውን እየነዳ ሲሄድ መሸና አሙማ ላይ ለምኖ አደረ፡፡ አሀያ እየነዳ በሚያድርበት ሁሉ ከጅብ ለመጠበቅ ከገዛበት ጊዜ አንስቶ አብሮ ደጅ ነው የሚያድረው፡፡ በማግስቱ ቤቱ አካባቢ ሲደርስ አሀያው መንገድ ላይ ተኛ፡፡ ቢለው ቢሰራው አልነሳ አለው፡፡ ለካስ ሞቷል፡፡ ገንዘብ ያበደረውን ወንድሙን ጠርቶ አሳየው፡፡ "በቃ ገንዘቡን ትቼልሃለሁ" አለው ገርቦሌ ግን አዘን የወጣ የወረደውን ካሀያ ጋር የተንከራተተውን አስቦ ጌታ ሆይ እንደማይሆን ለምን አልነገርከኝም አለ "ሙቼ ጠየከኝ" አለው ጌታም፡፡

"ከዚያ ጊዜ በኋላ እናቴ አገልግል መሶብ ሰፌድና ቁና በፍጥነት እንድሰፋ አደረገች፡፡" በማለት አዳነች ያን የችኮላ ግዜ ታስታውሳለች "ምነው እማ ለምንድነው" ብዬ ብጠይቃት "አንድ ላይ ሰብስበን ገበያ ወስደን እንሸጠዋለን" አለችኝ፡፡ ጎጆ መውጫዬ መሆኑን ያወቅሁት ኋላ ነው፡፡ በ1976 ዓ.ም ጀቢካ ላይ ኮንፈረንስ ተደርጎ ነበርና አባቴ ይዞኝ ወደ ኮንፈረንሱ ሄደ፡፡ የጋብቻችንን ጉዳይ የያዙት ሽማግሌዎችና ገርቦሌም እዚያው ነበሩ፡፡

በኮንፈረንሱ ማብቂያ ላይ ፊንጠር ብለው ከአባቴ ጋር ከተወያዩ በኃላ የሠርጉን ቀን ቆርጠው ተለያዩ፡፡ ከሁለት ሳምንት





በኋላ እንዲሆን ተወስኖ ወደቤት ተመለስን፡፡ በዚያው ሰሞን አዳዲስ ልብስ ተገዛልኝ፡፡ ለምን እንደሆን ለኔ አይነገርም የጎረቤት ልጆች እንደሚሉት ከሆነ "ልታገቢ ነው" ይላሉ፡፡ ስሰማ ወላጆቼ ላይ አለቀስኩ ለምን ትድሩኛላችሁ ጠልታችሁኝ ነው ብዬ ጠየኩ፡፡ "አልጠላንሽም ልጅ ማግባት ሕግ ስለሆነ ነው የምታገቢው" አሉኝና በዚህ ዓይነት ተዳርኩ፡፡ ከኛ ቤት እስከ ሙሽራውቤት የስድስት ሰዓት መንገድ ሲሆን በስልግ ዘጠኝ በቅሎ ታጅበን ተጓዝን፡፡ ባገራችን ይህን ያህል አጃቢ በቅሎ ለማንም ሰርግ ወጥቶ አያውቅም እንደውም አጎቴ "የሁለት ሠርግ አጃቢ ተደባልቆ ነው የመጣው ያዘጋጀነው ለዚሁ ሁሉ እንዴት ይበቃል ብሎ አባቴን ቢጠይቅ "በሉ አስገቧቸው ያለውን ጌታ ይባርክልናል" እንዳሉት ተረፈ እንጂ አልጎደለም፡፡

ግርግሩ ካለፈ በኋላ አዲሶቹ ባለትዳሮች ገርቦሌና አዳነች በግላቸው ኑሮን መግፋት ጀመሩ፡፡ ወንድሞቹ ቆርሰው የሰጡትን መሬት በዶማም በበሬም ሲገኝ እየለመነ በማረስ ግብርናውን ተያያዘው፡፡ ምንጭ ስለነበረው በበጋውም በመስኖ በቆሎ ይዘራበታል፡፡ ወንድሞቹ እንደተቃናለት ሲያዩ በመስኖ የሚለማውን መሬት ነጠቁትና በምትኩ በክረምት ብቻ የሚዘራበት ደረቅ ቦታ ሰጡት፡፡ "ሎጥ የለመለመውን ሲወስድ አብርሃምን በደረቅ ቦታ የተገናኘና የባረከ አምላክ ከኛ ጋር ነው በማለት በደረቁ ድርሻቸው ላይ ቆመው እግዚአብሔርን ጠሩ፡፡ እግዚአብሔርም ሰማ ለተገፉት ምንጭ ፈለቀና ደረቁ ድርሻቸው ለመለመ፡፡ የመስኖ ቦታ ሆነ፡፡

ምንጭ ከመነጨበት አዲሱ ድርሻቸው ላይ ሦስትና አራት ሰብል እንደሰበሰቡ የዘሩትን ሳይነሱ ባንድ በኩል ከአካባቢው ሕዝብ የተነሳው ስደት በሌላ በኩል የወንድሞቹ ግፊት ከዚያ ለቆ እንዲወጣ አስገደደው፡፡ በ1979 ዓ.ም የመጀመሪያዋን ልጃቸውን ኬናን ይዘው ከሊሊቱ በዘጠኝ ሰዓት ከአካባቢው በመሰወር ወጡ፡፡ አዳነች ቤተሰብ ዘንድ ጥቂት ከቆዩ በኋላ ወደ ደገም ሄዱ፡፡ የደገም አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ዳይሬክተር ገርቦሌን ቀደም ሲል ያውቀው ስለነበር በዘበኝነት ቀጠረው፡፡ እናም ገርቦሌ የት/ቤት ዘበኛ ሆኖ ከት/ቤቱ ግቢ ለዘበኛ የተሰራችው ቤት ውስጥ አዳነችንና ኬናን ይዞ ገባ፡፡

"ወደ ቤተሰብህ ሂደህ እደግ" ተብሎ ወገኖች በብዙ እንባ አዳንዶችም ያላቸውን ሳንቲም እያዋጡ ሰጥተውት ከሄደ በኋላ አገልግሎትም አቁሟል፡፡ ወደ አባይ እየወረደ ጥጥና ቅል የሚነግድ በመምሰል በተናጠል ለሚያገኛው ወንጌልን ሰብኳል፡፡" ሰዎች አልሰማ ብለዋልና እናንተ ዛፎች የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ በማለት ለጫካ የሰበከው በዚያ ዘመን ነው፡፡ "እናንተ ዛፎች እናንተ ድንጋዮች ምስክር ትሆናላችሁ ነገ ወደ ታላቅ የሰዎች ኮንፈራንስነት ትለወጣላችሁ" በማለት በልቡ ሞልቶ የሚፈሰውን የእግዚአብሔርን ቃል በውድማ ይሰብክ ነበር፡፡ አሁን ደገም ከመጣ በኋላ ግን ሊሊት ሊሊት ወደ ወገኖች ቤት በመሄድ ሰዎችን ማገልገል ጀምሯል፡፡ ቀስ በቀስ የአገልግሎት አድማሱ እየሰፋ ሲሄድ አርብ ማታ ጀምሮ ቅዳሜና እሁድን አገልግሎ ሰኞ ማለዳ ወደ ዘበኝነቱ ይመለሳል፡፡ እስኪመለስ ዘበኛዋ አዳነች ትሆናለች፡፡





ት/ቤቱ ትንሽ የእርሻ ቦታ ሰጥቷቸው ስለነበር በሬ ለምኖ በቆሎ ይዘራል፡፡ ከዚያ በኋላ ያለው የአረምና የጥበቃ ተግባር የአዳነች ነበር፡፡ ለዘበኝነት ሥራው የምትከፈለውን የተቸገረ ሰው ኪጋጠመው ሰጥቶ ባዶ እጁን የሚገባበት ጊዜ ጥቂት አልነበረም፡፡ እሷም ሊሊት በኩራዝ ስፌት እየሰፋች በመሸጥ ልጆቿን ለማሳደግ ትጥር ነበር፡፡ አዲሴና ዮናታን የተወለዱትም እዚሁ ደገም ት/ቤት ግቢ ውስጥ ነው፡፡ በዚህ በከፋ ችግር ውስጥ የሚመለከቱና የሚያውቋቸው ሰዎች "አንቺ በባዶ ሆድሽ ልጅ ከምታጠቢ ማርና ቅቤ ወደሚበላበት ያባትሽ ቤት ለምን አትመለሽም" ይሏታል፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ባልሽ ሲቸገር ወደ ወላጆችሽ ቤት ተመለሺ አይልም ቃል ኪዳናችን እስከ ሞት ስለሆነ ለሆዴ ብዬ ቃል ኪዳኔን አላፈርስም በማለት ትመልስላቸዋለች፡፡ አባቷ ገና ለገርቦሌ ሊሰጧት እንደወሰኑ አስቀምጠው የመከሯትን አትረሳም "ልጄ ይህ ሰው ሰማያዊ እንጂ ምድራዊ ሀብት የለውም እንደቃልህ የሚኖር ሰው ስጠኝ ብዬው የሰጠኝ ሰው ነው፡፡ ልጄ የኔ ሀብት ያንቺም ነው በርቺ" ብለዋታል፡፡

ባንድ በኩል ልጆች ይዞ ችግርና ርሃብ በሌላ በኩል ወደቤትሽ ተመለሺ በሚሉ መካሪዎች መሀል ለብዙ አመት ኖራለች ሁለተኛዋ ገርቦሌ፡፡ "እግዚአብሔር ቤታችን ባዶ መሆኑን ስለሚያውቅ እርሱን እጠብቃለሁ" እያለች ወላጆቿም ያላቸውን ጭነውም አሸክመውም ከመላክ ባለፈ አይዞሽ ባልሽ ራቁቱን የሆነው ለጌታ ብሎ ነው፡፡ ጥለሽ እንዳትመጪ በማለት ያበረታቷል፡፡ ከፉ የሚመክሯት የቅርብና ዝምድናም ያላቸው ጭምር በመሆናቸው ተስፋ

አይቆርጡም፡፡ ይባስ ብለው "እርሱስ አገልግሎት እያለ የሚሄደው አዲስ አበባ ሌላ የከተማ ሴት አግብቶ ነው፡፡ አንቺ በባዶ ቤት ትማቅቂያለሽ" አሏት፡፡ "ከፈለገ አንድ አይደለም አምስት ያግባ እኔ ስድስተኛ ሆኜ እኖራለሁ" ስትል እንቅጩን ነገረቻቸው፡፡

ያንጊዜ ጨው ውድ ነበር፡፡ የሚገዛውም ከህብረት ሱቅ በኮታ ሲሆን ከዕለታት አንድ ቀን አዳነች ልጅ አዝላ እንጀራ እየጋገረች ስለነበርና ባጋጣሚም ገርቢሌ እቤት ስለነበር "እባክህ ከህብረት ሱቅ ጨው ግዛተህልኝ ና!" ብላ ላከችው እሱ ወረፋውን ጠብቆ የተባለውን ጨው ገዝቶ ሲመጣ ገና ወረፋ የሚጠብቁ አቅመደካሞች ያይና ልቡ ይነካል፡፡ ስለዚህ ከያዘው ጨው ትንሽ ትንሽ እየቆነጠረ አካፍሎ ጨረሰውና ባዶ እጁን ገብቶ ዝም አለና ጥግ ላይ ተቀመጠ፡፡ "ገዛህ ወይ" ስትል ጠየቀችው የላከችው፡፡ አጎንብሶ ዝም አለ፡፡ ድጋሚ "ገርቢሌ ጨው ሰጡህ ወይ?" አሁንም ዝም ሲል ከዚህ በላይ መጠየቁ ስለከበዳትና ብዙ ጊዜም እሱን መጫን የማትወደው ባለቤቷ ተወችውና ሥራዋን ቀጠለች፡፡ ማታ የህብረት ሱቁ ሠራተኛ በደጃቸው ያልፍ ነበርና "ምነው አልመጣችሁም" በማለት ጨው ሰጥቷት አለፈ፡፡ ያውም በነፃ ሳያስከፍል ገርቢሌ ቀን ሄዶ ኮታቸውን ገዝቶ እንደወሰደ ረስቷል፡፡

ደግም በነበረበት ወቅት ወደ ገንጂ ቅዱሳንን ለመጎብኘትና ለማገልገል ጌታ ልኮት ሄዶ ነበር፡፡ ቦታው የአምስት ሰዓት መንገድ ሲሆን በዚያ ሰባት አማኞች ነበሩ፡፡ አራንዱፋና እናቱ አህቱና ጎረቤት፡፡ እነዚህን ጥቂት ሰዎች እንዲያገለግልና ወደፊት





የሚሆነውን ነግሯቸው እንዲመለስ መልዕክት ይዞ ስለነበር ምድሩ ላይ ፀልዮ "እዚህ ቦታ ቤተክርስቲያን ትተከላለች" ብሎ የመሰረት ድንጋይ ተክሎ "ነገ ተነገወዲያ የሚመጡትን ተቀበሉ" በማለት ከሰባቱ ሰዎች ሽማግሌ ገንዘብ ያዥና መዘምራን ሾሞ ፀልዮላቸው ተመለሰ፡፡ በርግጥ አሁን በዚያ ቦታ ትልቅ ቤተክርስቲያን አለ፡፡ እንደተባለውም ሕዝቡ ማንም ሳይጠራው ጌታን ፍለጋ ጎረፈ ምድሪቱም ከነበረባት ጨለማ ተላቀቀች፡፡ በጨለማ የኖረው ሕዝብ ብርሃን አየ በዚያም ተፈፀመ፡፡

ከጌታ የተሰጠውን ተልዕኮ ፈፅሞ እየተመለሰ ሳለ ደከመው ራበው፡፡ በኪሱ የነበረችው አንዲት ብር ብቻ ነበረች፡፡ ገዝቶ መብላት ቢፈልግ ከጥንቅሽ ያለፈ ምግብ አታመጣለትም፡፡ ድካም ብሶበት እግሩን ማንሳት ሲያቅተው ከመንገድ ዳር ወደ አንድ ዛፍ ስር ጠጋ አለና ግንዱን ተደግፎ "እፎይ" አለ፡፡ በዚያው እንቅልፍ ይዞት አልም አለ፡፡ በራዕይ አንድ ሰው ወደሱ ተጠግቶ "ተነስ ተነስና መንገድህን ቀጥል" አለው ማደር የነበረበት ቦታ ቀድሞውንም በጌታ የተዘጋጀ ስለነበር፡፡ ብንን ብሎ ሲነቃ አካባቢው ላይ አንዲት አሮጊት ቆመዋል፡፡ "እናቴ ምን ይሠራሉ" ብሎ ጠየቀ" ልለምን ነው የቆምኩት" ይሉታል፡፡ "እኔም እንደርስዎ ርቦኛል ጠምቶኛል ቁጭ ብዬ አለመንኩም እንጂ እኔም ችግረኛ ነኝ ይልቅስ ነጋዴዎች ከኋላ እየመጡ ስለሆነ ከነሱ መለመኑ ይሻላል" ብሎ መንገዱን ጀመረ፡፡ አሁንም አሮጊቷ "እኔ ከነጋዴዎቹ አለምንም የለመንኩት አንተን ነው የምትሰጠኝም አንተ ነህ" ይሉታል፡፡ "እረ እኔ ምንም የለኝ?" ይላል በማስተዛዘን፡፡ "አንድ ብርም የለህም?" በትክክል በኪሱ ያለችውን

አንድ ብር ማየት ከቻሉ ነገሩ ከጌታ ነው ብሎ አውጥቶ ሰጣቸውና በአሮጊቷ እየተገረመ መንገዱን ቀጠለ፡፡

በመንገድ ስለ አንድ ብሩ ያሰላስላል፡፡ "ጌታ ሆይ ለምን አትሰጣትም እኔ ምን አለኝና ወደ እኔ ትልካታለህ" ሲል ጠየቀ፡፡ "በማን ልስጣት የምሰጣት በአንተ በኩል ስለሆነ ነው" በማለት የጌታ መንፈስ መለሰለት፡፡ አሀ! እንደዚህ ነው ብሎ የወደፊት ጉዞውን ቀጠለ፡፡ ገሊሳ መሽቶ ደረሰ፡፡ እየዘነበበት ስለተጓዘ በስብሷል፡፡ መንገዱም በጭቃ ላቁጧል፡፡ መብረቅ ብልጭ ሲል መንገዱንና አካባቢውን እየለየ ሁለት ሰዓት ተኩል ሲሆን ወደ አንድ ቤት ተጠግቶ "እባካችሁ አሳድሩኝ የመሸብኝ መንገደኛ ነኝ" በማለት ልመናውን ወደ ተዘጋውና በየቀዳዳው የእሳት ጭላንጭል ወደሚፈነጥቀው ቤት ወረወረ፡፡ ወደ ባለቤቶቹ ጆሮ ድምፁ ከነቃላቱ ደርሶ ኖሮ "እናሳድርም እኛ ለራሳችን ችግር ላይ ነን፡፡ በቤታችን በሽተኛ ይዘን ቀንና ሌሊት እንሰቃያለን በሰላም የሚተኙ ሰዎች ቤት ፈልገህ እደር" በማለት ምላሽ ሰጡት፡፡ መንገደኛው ጥቂት አሰበ፡፡ በማታ ወንዶቹ የትሄደው ነው ወይስ ወንድ የለም፡፡ ፈርተውኝ ይሆን? ወይስ የታመመው አባወራው ይሆን" ለሁለተኛ ጊዜ "ግዴለም አሳድሩኝ እኔ ለበሽተኛ የሚሆን መድሃኒት አለኝ" ውስጥ ያሉት ጊዜ አልፈጁም በሩን ሲጢጥ አድርገው ከፈቱት፡፡ "ግባ" አስገቡት፡፡ እሳቱ ፏ ብሎ እየነደደ ነው፡፡ የቤቱ ባለቤት ምድጃው ዳር ሰሌን ላይ ተኝቷል፡፡ አይናገርም አይጋገርም በጣና ታሟል፡፡ በእሳቱ ብርሃን ሲታይ ባህር ገብቶ የወጣ ይመስል ከላይ እስከ ታች የበሰበሰው እንግዳ ወደ ተሰበሰቡት ቤተሰብ ዞር ብሎ





"እናንተ ምግብ አዘጋጁለት ወደዛ ቆዩ" በማለት ከበሽተኛው ገለል አደረጋቸው፡፡ ጠንቋይ ይሆን ወይስ ምንድነው ግራ ገባቸው፡፡ ጉስቁልናውና ባለመድሃኒት ነኝ ማለቱ አብረው አልሄድ አላቸው፡፡ ለማንኛውም ገለል አሉ፡፡ መንገደኛው ወደ ምድጃው በመጠጋቱ በውስጡ ሀሴት እያደረገ ወደ በሽተኛው ቀረበ፡፡ ቀስ ብሎ ወደተኛበት ጎንበስ አለና በጆሮው "ጌታ ኢየሱስ ያድንሀል በሽታህም ካንተ ይገፈፋል እንደሚፈውስህ እመንና አሁን ተነስተህ ቁም" ሲለው በሽተኛው ከእንቅልፍ የባነነ ያህል ብድግ አለና ቆመ መናገር ጀመረ "አንድ ሰው በእግሮቼ ላይ ተጠልቆ የነበረውን ነገር አወለቀልኝ ይኼው ዳንኩ ሲያወልቅልኝ ዳንኩ" እያለ መፈንጠዝ ጀመረ፡፡

ድንገት በሆነው ነገር ቤተሰቡ ተደነቀ ካሁን አሁን ይሞታል ብለው የሚጠብቁት አባወራ በደስታ "ዳንኩ፣ ዳንኩ" እያለ መላ አካሉን ሲዳስስ ከደስታ የተነሳ እየተጠመጠሙበት ያለቅሱ ጀመር፡፡ "አታልቅሱ ምግብ አምጡለት አንተም ተቀመጥ" "በማለት እንግዳው መድሀኒተኛ ሲናገር ወዲያው ታዘዙ ለገርቦሌ ጋቢ ወጣና ተደረበለት በጭቃ ለቦካው እግሩ ውሀ ቀረበ፡፡ ምግብ ቡና ተባለ የቤቱ አውድ ተለወጠ፡፡ ጥሩ ተደርጎ ተነጠፈለትና ተኛ፡፡ ለቁርስ ባለቤቱ መጥቶ እስከሚቀሰቅሰው እስከ ጧቱ ሁለት ሰዓት አልነቃም፡፡ ጥሩ ቁርስ ተበላ ቡና ተጠጣና ይህችን ለመንገድ ያዝ ብለው አስራ ሁለት ብር ስንቅ አሲዘው ሸኙት፡፡ ጉዞ ወደ ደገም ወደ ት/ቤቱ የጥበቃ ቤት፡፡

ሌላ ጊዜ ከአገልግሎት ወደ ደገም የጥበቃ ቤቱ ሲመለስ አንድ ክፉ ሰው በመንገድ ጠብቆ "አንተ የጴንጤ ካድሬ ሰውን ሁሉ እየመለመልክ ጨረስከው የሚያቆምህ ወንድ ጠፋ አይደለም ታየኛለህ እኔ አስቆምሃለሁ እገልሀለሁ" አለው፡፡ "እባክህ ወንድሜ እኔ ብመለምልም ለክፉ አልመለምልም ሰው ከክፉ ሥራው እንዲመለስ ነው የኔ ምልመላ ማንንም አይጎዳምና ተወኝ" በማለት ተለማመጠው፡፡ ፎካሪውም መልሶ "እዚህ አገር እንዲህ እያደረክ አትኖርም እገልሀለሁ" በማለት ከበፊቱ በበለጠ ደሙ ፈልቶ አፈጠጠበት፡፡ ሁለቱ እንደተፋጠጡ ተለማምጦ ማለፍ እንዳልተቻለ ገርቦሌ ሲገባው "ተው ትፀፀታለህ አትንካኝ" በማለት ከልመና ወደ ተመጣጣኝ ባላንጣነት በተሸጋገረ የድምፅ ቃና ተናገረው፡፡ "ሁለተኛ በዚህ መንገድ ስታልፍ ካየሁህ ውርድ ከራሴ ደምህ ደመከልብ ነው ማንም አይጠይቀኝም" በማለት ከፉኛ ዛተበት፡፡

የሰውየው ቤት በዚህ መንገድ ዳር ነው፡፡ መንገዱ ደግሞ አንድና ማሳበሪያ ስርጥ የሌለው በመሆኑ ለአገልጋዩ በዚያ የማለፍና ያለማለፍ ነገር ፈተና ሆነበት፡፡ ማገልገል ካለበት የሚወጣው የሚገባው በዚህ መንገድ ነው፡፡ አገልግሎቱን ካለ በዚህ ያልፋል ሕይወቱን ካለ ቤቱ ይቀመጣል፡፡ ስንት እንቅፋትና ወጥመድ አልፎ የመጣው የእግዚአብሔር ባሪያ እንዴት ፈርቶ ህይወቱን የሰጠለትን ተልዕኮ ያቆማል፡፡ ስለዚህ ጉዳዩ ወደ ጌታ መቅረብ ነበረበት "ጌታ ሆይ በየት ልለፍ እንዳያየኝ አሳውርልኝ" በማለት አቤቱታ አቀረበ፡፡ ዱታ ነኝ የሚለው ሰውዬ ታውሮ ማን ይምጣ ማን ይሂድ የማያውቅበት ጨለማ ሕይወት ውስጥ ገባ፡፡ ማለፊያ ያጣውም ሰው





ወሬውን አጣርቶ እውነትነቱን ሲረዳ በዚያው መመላለሱን ቀጠለ፡፡ ሰውየው ከዐይኑ ተምሮ ንስሀ ቢገባ ቢልክበትም ጥሩ ነበር፡፡ አላደረገውምና በወሩ ሞተ፡፡

ደገም በነበረበት ጊዜ የሁለት መንግስት ሠራተኛ ሆኖ አገልግሏል ለምድራዊው መንግስት የጥበቃ ሠራተኛ ለሰማያዊው መንግስት የዚያ ቦታ የወንጌል አገልጋይ በመሆን፡፡ ማታ ተማሪዎች ከወጡ በኋላና ጧትም ሳይገቡ በፊት በዴስኮቹ ላይ እጁን እየጫነ "ጌታ ሆይ በነዚህ መቀመጫዎች ላይ ተቀምጠው የሚማሩትን እነዚህን ልጆች ባርካቸው፡፡ ያንተ ፍርሃት ይግዛቸው የሚያውቁህና የሚገዙልህ ይሁኑ ለሀገራቸው የሚጠቅሙና ለቁም ነገር የሚበቁ አድርጋቸው" በማለት እነዚያን በዝቅተኛ ኑሮ የሚገኙ የገበሬ ልጆች ለእግዚአብሔር አደራ አሳልፎ ይሰጣል፡፡ ለመምህራኑና ለሠራተኞቹም እንዲሁ፡፡ በዘመኑ ከነገሰው የክህደት አስተሳሰብ ተላቀውና ካኪ ለብሰው ፍንጥር ፍንጥር ማለቱን ትተው ራሳቸውን የሚያውቁና የሚገዙ ትውልድን ቀራፂ በመሆን ለአምላክ የሚገዙ እንዲሆኑ ለጌታ አደራ ይሰጣቸዋል፡፡ ጌታም አደራን የሚያከብርና የሚጠብቅ ነውና ከነዚያ ተማሪዎች ብዙዎቹ ተምረው ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሰዋል፡፡ ቤተሰቦቻቸውን ሳይቀር ከዚያ ያወጡና አዲስ አበባ ቤት ሠርተው ያስቀመጡ ውጪ ያወጡም አሉ፡፡ መምህራኑም ቢሆኑ ብዙዎቹ በጌታም በህይወትም አሉ ዳይሬክተሩን ጨምሮ፡፡

ተማሪዎች ሲያረፍዱ ቀጥቶና መክሮ እንዲያስገባ በር ላይ ለሚጠብቀው የጥበቃ ሠራተኛ ከዳይሬክተሩ ይታዘዛል፡፡ ገርቦሌ

ያረፈዱትን ልጆች ከቅጣት ምክር ስለሚቀድም "ጌታን ትወዳላችሁ ተቀበሉት እሱ ይወዳችኋል ጥሩና ታላቅ ሰው ያደርጋችኋል" ይላቸዋል፡፡ በመጨረሻም ተመክረዋል ብሎ ያሳልፋቸውና ወደክፍላቸው ይገባሉ፡፡ በየቀኑ ምክሩን (ወንጌልን) ከሱ ለመስማት ሆን ብለው የሚያረፍዱም ነበሩ፡፡

የሦስት አመቱ የደገም ቆይታው ዘበኛ ይባል እንጂ እንደገና ወደ አገልግሎት የተመለሰበት ጊዜ ነበር፡፡ ሌሊት እየዞረ ያገለግላል ቅዳሜና እሁድ ርቆ በመሄድ ያገለግላል፡፡ ባዶውን ክፍል ልክ በሰው እንደተሞላ አዳራሽ በመቁጠር ይሰብካል፡፡ ከዚያም ባለፈ ለታመሙ ተማሪዎች ወላጆችና ያካባቢ ነዋሪዎች ህመም ይፀልያል፡፡ የተጨነቁ ሰዎች ያለበት ድረስ በሽተኞችን ተሸክመው ያመጡ ነበር፡፡ ጌታም ይፈውሳቸው ነበር፡፡





# ሌላ ትልቅ ስራ

በ1982 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ በአንድ ሌሊት ገርቦሌና አዳነች ተመሳሳይ ህልም አይተው አደሩ፡፡ ህልሙም ሦስት ነጭ የለበሱ ሰዎች ወደቤታቸው መጥተው "አሁን ይበቃል የዚህ ቦታ ቆይታህ አልቋልና ከዚህ በኋላ ሌላ ትልቅ ሥራ ስለተዘጋጀ ወደዚያ ትሄዳለህ" የሚል ነበር፡፡ ባልና ሚስት ስለ ህልማቸው እየተገረሙ ሳለ የአዳነች ወንድም ገመቹ ቶሌራ ከነቀምት ሙሉ ወንጌል ቤተክርስቲያን ተልኮ ነበርና መልዕክት ይዞ መጣ፡፡ በዚያን ጊዜ የነቀምት ሙሉ ወንጌል ቤተክርስቲያን መሪዎች የነበሩት እነ ፓስተር ተስፋዬ ራዕይ ያለውና ጌታ የጠራው አገልጋይ ይፈልጉ ኖሯል፡፡ በዚህ መሀል አንድ እግዚአብሔር የጠራው ነገር ግን የተጣለና አሁን ዘበኛ ሆኖ የሚኖር ሰው ደገም ላይ እንዳለ ይሰማሉ፡፡ ይኼኔ ነው ያመልዕክተኛ ገርቦሌን ወደነቀምት ሙሉ ወንጌል ቤተክርስቲያን እንዲጠራ ተልኮ የመጣው፡፡ የገርቦሌን መሳፈሪያ ፓ/ር ተስፋዬ ኃይሌ ከራሳቸው ኪስ ሲልኩ ገመቹ ቶሌራ ደግሞ ሠራተኛ ስለነበር የራሱን መሳፈሪያ ችሎ ወደ ጊዳ ተጓዘ፡፡

ይህ የተረጋገጠ የእግዚአብሔር ፈቃድ በመሆኑ ከደገም ነቅሎ ወደ በካቀሌ ለመጓዝ ጊዜ አልፈጀበትም፡፡ ቀሌ በደርግ ዘመን በገበሬዎች መንደር ምሥረታ የተቋቋመች መንደር ስትሆን ቀስ በቀስ ገበሬዎቹ ከመንደር ምስረታው ሰፈር እየተንሸራተቱ ወደ ቀድሞው ቆዬና ከሲ ጓሮ በመመለሳቸው ብዙ ባዶ ጎጆዎች በቀሌ ነበሩ፡፡ እነ ገርቦሌም ወደ አንዱ ባዶ የሳር ክዳን ቤት ገብተው